አዲስ ዘመን
እንድ
ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 243 ግንቦት 3 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# “በመሠረታዊ ሸቀጦች ራስን ለመቻል እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ርብርብ ሊያደርግ ይገባል”

- ብሔራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ምክር ቤት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፦ በመሠረታዊ ሸቀጦች ራስን ለመቻል በምንወስዳቸው ርምጃዎች እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ርብርብ ሊያደርግ ይገባል ሲል ብሔራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ምክር ቤት አሳሰበ።

ብሔራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ምክር ቤቱ የ2014 የበጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የኢኮኖሚ አፈጻጸምን በማስመልከት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በበጋ ስንዴ ምርት ላይ የታየውን አበረታች ውጤት በማጎልበት በመሠረታዊ ሸቀጦች ራስን ለመቻል በምንወስዳቸው ርምጃዎች እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ርብርብ ሊያደርግ ይገባል።

ጥረታችን ኢኮኖሚው ተግዳሮቶችን ከመቋቋም አልፎ ተግዳሮቶችን ወደማሸነፍ የሚያሸጋግር መሆን አለበት ያለው መግለጫው፤ መንግሥት፣ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ፣ ምሁራንና ሕዝቡ፣ ሁሉም የየድርሻቸውን መወጣት ከቻለ በእርግጥም ጥረታችን ፍሬ ማፍራቱ አይቀርም ብሏል።

በእስካሁኑ ጉዞአችን የገጠሙን ፈተናዎች ጥንካሬአችንን የተገዳደሩ ቢሆኑም በቀላሉ ስላልወደቅን አጠንክረውን አልፈዋል። ፈተናዎቻችንን በጽናት ተቋቁመን ባለፍን ቁጥር አንድ ደረጃ ወደ ላይ ከፍ ማለታችን አይቀርም፤ የሚለው ብሔራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ምክር ቤቱ መግለጫ፤ የምናስመዘግባቸው ድሎች በሚፈጥሩልን ወኔ ተበረታትተን አሻግረን የብልጽግና ተስፋችንን እንደምናይ ምንም ጥርጥር የለውም። ተስፋችን ተሳክቶ ለትውልዱ የበለጸገች ኢትዮጵያን ማውረስ እንድንችል እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የበኩሉን ትብብር እንዲያደርግ በዚህ አጋጣሚ ጥሪያችንን እናቀርባለን ሲል አስታውቋል።

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሩብ ዓመታት ላይ የተመዘገበው ዕድገት ላይ በመንተራስ የዓመቱ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በአማካይ በ6 ነጥብ 6 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው የሚጠበቅ መሆኑን አመልክቶ፥

“በመሠረታዊ ሸቀጦች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ፎቶ፦ፀሐይ ንጉሴ

# ማንነትን የማጥፋት የግፍ ተግባር በወልቃይት

**ወርቁ ማሩ**

አሸባሪው ሕወሓት በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ ላለፉት አርባ ዓመታት በፈፀመው ስልታዊና የተቀናጀ የዘር ማፅዳት ወንጀል ከእያንዳንዱ ቤተሰብ 29 ከመቶ ለህልፈት፣ 26 ነጥብ 5 ከመቶ ለስደት መብቃቱንና 19ነጥብ 5 ከመቶ ደግሞ የት እንደገባ እስካሁን እንደማይታወቅ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጥናት አመላከቷል። 12 የጅምላ መቃብር ቀጠናዎች መገኘታቸውንም አስታውቋል። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ይህን መነሻ በማድረግ ጉዳዩን ከምንጩ ለማጣራት የጋዜጠኛ ቡድን ወደስፍራው ልኳል።

የጋዜጠኞቹ ቡድን ጅምላ ጭፍጨፋ ተፈፅሞባቸዋል ከተባሉ ስፍራዎች ውስጥ በወልቃይት ወረዳ ደጀና የተባለ ስፍራ በመገኘትም የአካባቢውን ማኅበረሰብ፣ የአስተዳደር አካላት፣ የዓይን ምስክሮች እንዲሁም የተጎጂ

ማንነትን የማጥፋት ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# «ወራሪው ቡድን ከጥፋት መንገዱ እንዲታቀብ የትግራይ ሕዝብና ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ሀይ ሊሉት ይገባል»

- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን

**መሳኩ ኤሮሴ**



ባህር ዳር፦ ወራሪው የሕወሓት ቡድን በአሁኑ ወቅት ለዳግም ጥፋት ከሚያደርገው እንቅስቃሴ እንዲታቀብ የትግራይ ሕዝብና ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ሀይ ሊሉት እንደሚገባ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ጠቆሙ።

የአማራ ክልል «በሕግ ማስከበርና በህልውና ዘመቻ የተከፈለ መስዋዕትነት ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና አንድነት» በሚል መሪ ሃሳብ የዕውቅናና የምስጋና ፕሮግራም ባህር ዳር ከተማ ትናንትና አካሂዷል።

በወቅቱ አቶ ደመቀ መኮንን እንደተናገሩት፤ ወራሪው የሕወሓት ቡድን ለዓመታት ከቆየበት የጥፋት መንገዱ እንዲታቀብ የትግራይ ሕዝብና ዓለም አቀፍ ተቋማት በቃ ሊሉት ይገባል።

የኢትዮጵያን የብልፅግና ጉዞ ለማደናቀፍ ጠላቶች

«ወራሪው ቡድን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ማንነትን የማጥፋት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ቤተሰቦችን አነጋግሯል። አሸባሪው ሕወሓት በግፍ ከጨፈጨፋቸው የአካባቢው ተወላጆች መካከል ማሳያ የሚሆነውን በአባ ልጃለምና ቤተሰባቸው ላይ የደረሰውን ግፍና የዘር ማጥፋት ተግባር አንዱ ነው።

## አባ ልጃለም ታዬ ማናቸው?




አባ ልጃለም ታዬ ትውልዳቸውም ሆነ እድገታቸው በወልቃይት ወረዳ ደጀና አካባቢ ነው። አባ ልጃለም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሚከበሩ እና የሚወደዱ ሰው ሲሆኑ የታሪክ አዋቂም ናቸው። ስለእውነት ከመናገር የማያቅማሙ የመርህ ሰውም ናቸው። በዚህ የተነሳ የአካባቢው ነዋሪ ሁሉ ለቃላቸው ይገዛል፤ ተምሳሌትነታቸውንም ይከተላል።

እንደ አካባቢው ነዋሪዎች ገለጻ ታታሪ አርሶ አደርነታቸው ከአካባቢው ለምነት ጋር ተዳምሮ ጥሩ ሀብትና ንብረት እንዲያፈሩም አስችሏቸዋል። የተከሏቸው ዛፎች ጭምር «የነአባ ልጃለም ሰፈር» የሚል ስያሜን አሰጥቷቸዋል። ግቢአቸውና ደጃፋቸው በእንክብካቤ የተያዘ በመሆኑም ወደ መኖሪያ ቀዬአቸው ሲደረስ የምድር ገነትን የጎበኙ እስኪመስል ድረስ ሀሴትን ያጎናጽፋል። ልጆቻቸውም ቢሆኑ ገና ከለጋ ዕድሜአቸው ጀምሮ በሥራ ትጋትና በመልካም ሥነምግባር ያደጉ በመሆኑ ቤተሰቡ ሁሉ ደስተኛ ኑሮ ይኖራል።

የአካባቢው ማኅበረሰብ በችግሩም ሆነ በደስታው ጊዜ የአባ ልጃለምን ሃሳብ መፈለጉ የተለመደ ነው። በአካባቢው ግጭቶች ሲከሰቱ በማስታረቁ ረገድ ትልቅ ሚና ያላቸው እሳቸው ናቸው። ትዳር የሚፈልጉ የአካባቢው ነዋሪዎችም ቢሆኑ አባ ልጃለም የሌሉበት ሽምግልና አይደምቅም ይላሉ። ከዚህም ባሻገር እሳቸው ያሉበት ስብሰባም ሆነ የምክክር መድረግ በስምምነት መካሄዱ የተለመደ ነው። ምክንያቱም በሳልና የአካባቢው ራስ ናቸውና። በዚህ የተነሳ ደጀና ሲነሳ የአባ ልጃለም ስም በጉልህ መነሳቱ አይቀሬ ነው።

## የሕወሓት እና የወልቃይት ጠገዴ ትውውቅ



የወልቃይትና የትግራይ ሕዝብ ግንኙነት ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ፤ መረጃዎችም ይጠቁማሉ። በተለይ ቀደም ባለው ዘመን በርካታ የትግራይ ተወላጆች ወደ ወልቃይት በመሄድ የተለያዩ የጉልበት ሥራዎችን ሠርተው ተከዜ ሳይሞላ ወደ አካባቢያቸው ይመለሱ እንደነበር ይገልጻል።

ልዑል ራስ መንገሻ ስዩም የሕይወት ታሪካቸውን በተመለከተ ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ፣ ሁመራን ጭምር በስሩ የሚያቅፈውን የወገራ አውራጃን ይገዙ የነበሩት ቢትወደድ አዳነ መኮንን አስመራ ላይ በተካሄደ ኤክስፖ ላይ ባቀረቡት መነሻ ሃሳብ በየዓመቱ 40 ሺህ የሚሆን የትግራይ ሕዝብ ወደ ሁመራ እየሄደ ሲሠራ ከርሞ ወደ ትግራይ ሲመለስ ይፈጅበት የነበረውን ረጅም ጉዞ ለማሳጠር ይቻል ዘንድ መንገድ እንዲሠራላቸው ጠይቀው እንደነበር ጠቅሰዋል።

በ1972ዓ.ም የወልቃይት ወረዳ አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ተስፉ የሺወንድም እንደሚገልጹት የወልቃይት፣ ጠገዴና ሁመራ አካባቢ የለም መሬት ባለሀብት በመሆኑ አርሶ አደሩ በርካታ እርሻ ነበረው። በዚህ የተነሳ የአካባቢው አርሶ አደር ገንዘብ እየከፈለ ከትግራይ የሚመጡ የጉልበት ሠራተኞችን ያሠራ ነበር። እነሱም እህል ከተሰበሰበ በኋላ ተከዜ ሳይሞላ ተሻግረው ይሄዳሉ።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በወልቃይት፤ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ የተፈፀመውን ጅምላ ጭፍጨፋ በተመለከተ ያካሄደውን ጥናት የመሩት ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ አስራደ እንደገለፁት፣ አካባቢው በርካታ እንስሳት የሚረቡበት እና ሰሊጥና ጥጥን ጨምሮ በርካታ ሰብሎች የሚመረቱበት ለም አካባቢ ነው። በመሆኑም ሕወሓት ታላቋን ትግራይ ለመመስረት ሲያስብ ይህን አካባቢ መቆጣጠር እንደሚገባ በማመን ለዚህ ሲሠራ ኖሯል ይላሉ።

በሌላ በኩል አካባቢው ከኤርትራና ከሱዳን ጋር የሚዋሰን በመሆኑ ሕወሓት ላለመው ታላቋ ትግራይን የመመስረት ዓላማ ኮሪደር ለማግኘት ይህ አካባቢ ወሳኝ ነው። በዚህ የተነሳ ገና ወደስልጣን ሳይወጣ ጀምሮ ኮሪደር ማግኘት አንዱ ግቡ አድርጎ ሲንቀሳቀስ መቆየቱንና ይህ አካባቢ ከሱዳን ጋር የሚያገናኘው በመሆኑ የትኩረቱ መነሻ እንደሆነም ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ አመላክተዋል።

ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ በአንድ ወቅት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የማንነት ጥያቄ ይመለስልን በሚል ከወልቃይት ሕዝብ ለቀረበላቸው ጥያቄ «እኛ በጉልበት ነው የያዝነው፤ እናንተም ከቻላችሁ በጉልበት መያዝ ትችላላችሁ» የሚል ምላሽ እንደሰጧቸውም ጠቁመዋል። ይህም የሕዝቡን ጥያቄ በሕጋዊ መንገድ መመለስ አዳጋች በመሆኑ በጉልበት ወደ ማስፈራራት መሄዳቸውን ያሳያል ብለዋል።

## ሕወሓት እና ወልቃይት



ሕወሓት የወልቃይት አካባቢን መውረር የጀመረው በ1972ዓ.ም እንደሆነ በወቅቱ የወልቃይት ወረዳ አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ተስፉ የሺወንድም ይገልጻሉ። ሆኖም ሕዝቡ ሕወሓትን ባለመቀበሉ በአጭር ጊዜ ተባሮ ሊወጣ ችሏል። በዚህ ቂም የያዘው ሕወሓት ዳግም አቅሙን በማጠናከር በ1974 ዓ.ም አካባቢውን ተቆጣጠረ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ላለፉት አርባ ዓመታት የሕዝቡን ማንነትና ሀብቱን ቀምቶ ኖሯል።

በተለይ በ1983 ዓ.ም የመንግሥትነት ስልጣን ሲያገኝ የመጀመሪያ አጀንዳው በማድረግ በካርታ ጭምር አስደግፎና ራሱ በቀረጸውና ራሱ ባፀደቀው ሕገመንግሥት ወልቃይትና ጠለምትን በትግራይ ክልል አካቶ እንደጠቀለለው አቶ ተስፉ ጠቅሰዋል።

ነገር ግን የወልቃይት ሕዝብ የሕወሓትን ድርጊት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይቃወም ነበር። «ወልቃይት የአማራ እንጂ የትግራይ አካል ሆኖ አያውቅም» «ወልቃይት፣ ሁመራም ሆነ ጠለምት አማራ ነው፤ ማንነታችን ይመለስ» የሚለው ጥያቄ በሕዝቡ ዘንድ በየጊዜው ይነሳ ነበር።

«ዳገት ያበረታው የአማራ ፍኖት» በሚል የወልቃይትን ጉዳይ በተመለከተ ታሪክ ነክ መጽሐፍ ለንባብ ያበቁት አቶ ቹቹ አለባቸው ከአንድ ዓመት በፊት ከአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለፁት፣ የወልቃይት ሕዝብ ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ ሕወሓትን ሲታገል ነው የኖረው።

ሕወሓት አማራን በስነልቦናና በኢኮኖሚ የመጉዳት እና ባህሉን የማዳከም ኢላማ ይዞ ሲሠራ ኖሯል ያሉት አቶ ቹቹ ለዚህም ማሸማቀቅ እና አንገቱን ማስደፋት ዋነኛ ስልቱ ነበር ብለዋል። ባለፉት አርባ ዓመታትም ከ500 ሺህ እስከ 700 ሺህ የሚሆን የወልቃይት ሕዝብ በሕወሓት የተነሳ ከቀየው ተፈናቅሏል ብለዋል።

«ወልቃይት ለአማራ ታሪኩ፤ የባህር በሩና የኢኮኖሚ መሠረቱ ነው» ያሉት አቶ ቹቹ፣ ሕወሓት ይህንን ማንነቱን ለመቀማት ከፍተኛ ሥራ ሲሠራ መኖሩንም አብራርተዋል።

ሕወሓት የሕዝብ ጥያቄን ለመቀልበስና ወልቃይት የትግራይ አካል መሆኑን ለማሳመን ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎችን፣ የሃይማኖት አባቶችና ታሪክ አዋቂዎችን ሁሉ እየፈለገ ሕዝቡን እንዲያሳምኑ ጠየቀ፣ ከፊሎቹንም በማስፈራራት ለማሳመን ሞከረ። ነገር ግን አንዳቸውም ይህን ያፈጠጠ የውሸት ትርክት ሊቀበሉ እንዳልቻሉ አቶ ተስፉ ይናገራሉ። እሳቸውም በዚህ የተነሳ አገራቸውን ጥለው ከተሰደዱ የአካባቢው ነዋሪዎች አንዱ ሆነዋል።

በዚህ መልኩ የሕወሓትን ድርጊት ከተቃወሙ የአካባቢው ታዋቂ ሰዎች ውስጥ አንዱ ደግሞ አባ ልጃለም ታዬ ናቸው። አባ ልጃለም ወልቃይት አማራ እንጂ ትግራይ ሆኖ አያውቅም የሚለውን አስተሳሰብ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ያንፀባርቁ ነበር። ይህ ታዲያ በሕወሓት ጥርስ ውስጥ እንዲገቡ አደረጋቸው። ሊበቀሏቸውም ተነሱ።

## በነአባ ልጃለም ላይ የተፈፀመው ግፍ



የአባ ልጃለም የልጅ ልጅ የሆነው አቶ ተመስገን በራ እንደሚለው አባ ልጃለም ለዘመናት የኖሩበትን የወልቃይት አካባቢ ማንነት ለመለወጥ የተጀመረው ነገር ፈጽሞ የማይሆን መሆኑን በመግለጽ ሕወሓት ከዚህ ተግባር እንዲታቀብ አሳሰቧቸው። ወልቃይት የአማራ እንጂ የትግራይ አካል ሆኖ እንደማያውቅም ታሪክ ጠቅሰው ሞገቷቸው።

ይህ ግን ለሕወሓት ትልቅ የራስ ምታት ነበር። በዚህ የተነሳ ይህንን ሃሳባቸውን ለማስቀየር አንዴ በሰላማዊ መንገድ፤ ሌላ ጊዜ በማስፈራራት በርካታ ጥረቶችን አደረጉ። ከዚያ በኋላ የእሳቸውን አለመቀበል ሲመለከቱ በ1978 ዓ.ም ባዶ ስድስት ወደሚባል እስር ቤት አስገቧቸው። በዚያ ለስድስት ዓመታት ቆይተዋል። በእስር ቤት ቆይታቸውም በርካታ ግፎች ተፈፅሞባቸዋል። በእስር ቤት ውስጥ ሁሉንም ዓይነት የግፍ መንገዶች በመጠቀም አሰቃይተዋቸዋል።

ግፉ በዚህ ብቻ አላበቃም። ከዚያ በኋላ ስቃዩ እንደውርስ ወደ ልጆቻቸውና ሌሎች ቤተዘመዶቻቸው ዞረ። የቤተሰቡን ንብረት በመውረስ ወደድህነት እንዲገቡ አደረጉ። ሌላው ቀርቶ ዛፎቻቸው እንኳን ከግፉ አላመለጡም። እኒያ እንደልጆቻቸው የሚወዷቸውና ተንከባክበው ያሳደጓቸው ዛፎች የጥፋ ምሳር አረፈባቸው። የእነዚህ ዛፎች ቅሪት ዛሬም ህያው ምስክር ሆኖ ለታሪክ ተቀምጧል።

አቶ ተመስገን እንደሚለው በወቅቱ አልጋ ላይ መተኛት የለባችሁም በማለት አልጋቸውን እና የሚተኙበትን መኝታ ጭምር ጭነው ወስደዋል። ጥረው ግረው ንብረት ሲያፈሩም በየዓመቱ እየጠበቁ ለአራት ዓመታት ዝርፊያ ፈጽመውባቸዋል።

ልጃቸው አቶ አዲሰይም የአባቱ መንገላታት ከአቅሙ በላይ ሲሆንበት ወደጫካ በመግባቱ እሱን ካላመጣችሁ አንዳችሁም በሕይወት አትኖሩም በሚል በዛቻና በማስፈራራት እንዲሁም ከፍተኛ ስቃይ በመፈፀም እንዳሰቃዩአቸው አቶ ተመስገን ይናገራል። ከዚህ በኋላ አባ ልጃለም እስከእለተ ሞታቸውም ድረስ በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ ኖረው በመጨረሻ ማለፋቸውን ይናገራል።

ከዚያ በኋላ በ1984 ዓ.ም አለምሸት ልጃለም ታዬ፣ በ1988 ዓ.ም ደግሞ አዲሰይ ልጃለም ታዬ የተባሉ ልጆቻቸው የሕወሓት ካድሬዎች የግፍ ጭካኔ ሰለባ ሆኑ። ሌላኛው ልጃቸው ወጣት ተክሌ ልጃለም ደግሞ በዳንሻ እስር ቤት ከታሰረ በኋላ የት እንደገባ እስከመጨረሻው ድረስ ሳይታወቅ ኖሯል፤ ዛሬም ቢሆን ይኑር ይሙት የሚያውቅ የለም።

አቶ ተስፉ እንደሚሉት ሕወሓት በዚያን ጊዜ በተለይ የአካባቢውን ተወላጆች ከአካባቢው በማፈናቀል እና የሕወሓት ታጋዮችን በቦታው ላይ በማስፈር የሕዝብ አሰፋፈር ሥርዓቱን ለመቀየር ከፍተኛ ሥራ መሥራቱን ተናግረዋል።

ከዚህም አልፎ በተለይ ታሪክን የሚያውቁ የአካባቢው ነዋሪዎችን እየፈለገ ያጠፋቸው እንደነበር የገለፁት አቶ ተስፉ በዚህ የተነሳ በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎች ተገድለዋል፤ ከፊሎቹም ተፈናቅለዋል፤ ብዙዎች ደግሞ ከሀገር ተሰደዋል ብለዋል።

## አቶ ስብሃት ነጋ በወልቃይት



አባ ልጃለም በባዶ ስድስት ውስጥ በታሰሩበት ወቅት በሕወሓት ካድሬዎች ብዙ መከራና ግፍ ቢፈጸምባቸውም ወልቃይት የትግራይ አካል ነው የሚለውን ሃሳብ ሊቀበሉ አልፈለጉም። የዱላ መብዛትም ሆነ የዘመዶቻቸው ስቃይ ከዚህ ሃሳባቸው ፍንክች አላደረጋቸውም። ለመጨረሻ ጊዜ ሃሳባቸውን ለማስቀየር የሕወሓት የነፍስ አባት የሆኑት አቦይ ስብሃት ነጋ ወደ ስፍራው ተልከው እንደነበር የልጅ ልጃቸው አቶ ተመስገን በራ ይናገራል።

አቶ ተመስገን እንደሚለው በ1984 ዓ.ም ክረምት ላይ አቶ ስብሃት ነጋ በደጀና ባዶ ስድስት ተገኙ። ዋነኛ ዓላማቸውም አባ ልጃለምን በማስፈራራት አልያም በማግባባት ማሳመን ነበር። ነገር ግን አባ ልጃለም ማንነታቸውን እንደማይክዱ ለአቦይ ስብሃት እቅጩን ነገሯቸው። ይህ አቦይ ስብሃትንም ሆነ የሕወሓት ካድሬዎችን ተስፋ ያስቆረጠ የመጨረሻ ሙከራ ነበር።

በዚህም መነሻነት አቦይ ስብሃት ተስፋ ቆርጠውና ጭካኔ ጨምረው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ፤ ከዚያ አባ ልጃለምም ከእስር እንዲወጡ ተደረገ። ነገር ግን ከእስር ቤቱ የወጡት በሰላም አልነበረም። በመርፌ በተሰጣቸው መድኃኒት አንደበታቸው ተዘግቶ እና ግማሽ አካላቸው መንቀሳቀስ እንዳይችል ተደርጎ ነው። በዚህ መልኩ ለብዙ ጊዜ ሲሰቃዩ ቆይተውም በ1986ዓ.ም ሕይወታቸው ሲያልፍ ግፉ ግን በልጆቻቸውና በዘመዶቻቸው እንዲሁም በዛፎቻቸው ላይ ጭምር ቀጠለ።

## ዛፎችን መረሸን ከትናንት እስከዛሬ



አሸባሪው ሕወሓት በቅርቡ የአማራ ክልልን በወረረበት ወቅት በርካታ ግፎችን መፈፀሙ የሚታወስ ነው። በዚህም በርካታ ጅምላ ጭፍጨፋዎችን ፈጽሟል፤ አዛውንቶችን ሳይቀር ደፍሯል፤ ንብረት አውድሟል፤ እንስሳትንም ዘርፏል፤ መዝረፍ ያልቻለውን ደግሞ ገድሎ ጥሏል።

በዚህ መልኩ የሕወሓት የግፍ ሰለባ ከሆኑት ውስጥ ደግሞ ዛፎችም ይገኙበታል። ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በአንድ ወቅት እንደገለፁት፣ ሕወሓት ከአሸባሪም በላይ ነው።

ዲያቆን ዳንኤል እንደገለፁት፣ አሸባሪ የሚባሉ ሰዎች የሚረሽኑት ሰዎችን ነው፤ ሕወሓት ግን በመቄት እና በጭና ሦስት ነገሮችን ረሽኗል፤ ሰዎችን፣ እንስሳትን እና እፅዋትን። በሌላ አገር የአሸባሪ ታሪክ እንዲህ ዓይነት ተግባር ታይቶ አይታወቅም። ይህ ቡድን ዕድል ቢያገኝ በዓለም ላይ መልካም የተባሉ ነገሮችን ሁሉ ከማጥፋት ወደኋላ የሚል አይደለም።

ይህ ድርጊት ታዲያ አዲስ አለመሆኑንና ሕወሓት ከልጅነቱ ጀምሮ የኖረበት ባህርዬው እንደሆነ በነልጃለም ዛፎች ላይ የፈፀመው ጭፍጨፋ አመላካች ነው። በወቅቱ እነልጃለምን ለማዋረድና ወደ ድህነት ለመመለስ ሕወሓት ከተጠቀማቸው ስልቶች አንዱ ንብረታቸውን ማጥፋት ነበር። በዚህም የሚችለውን ሁሉ ዘርፎ ወስዷል። አቶ ተመስገን እንደሚለው አራት ዓመታት ያህል በየጊዜው እየተመላለሰ ንብረታቸውን ዘርፏል።

ይህም አልበቃ ብሎት ዛሬም ድረስ አሻራቸው የሚታየውንና የአባ ልጃለምን ደጅ ያደመቁት ትላልቅ ዛፎችም ላይ የጥፋት ምሳር አሳርፎባቸዋል። በሌላ ቋንቋ ረሽኗቸዋል።

በወቅቱ ዛፎቹ የተጨፈጨፉበት መንገድ ደግሞ መልሰው እንዳያድጉ ጭምር ከሥራቸው ጭምር በማጥፋት እንደነበር አቶ ተመስገን ይናገራል። ዛፎቹንም ቆርጠው እዚያው የጣሉአቸው በመሆኑ ዛሬም የዛፎቹ «ቅሪተ አፅም» ተጋድሞ ይታያል።

## ሰማዕታቱን የማስታወስ ተግባር



ለወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ ማንነት ሲሉ ሕይወታቸውን የገበሩት የአባ ልጃለም ልጆች አፅም በክብር የማሳረፍ ሥነሥርዓት ሚያዝያ 7 ቀን 2014 ዓ.ም በወልቃይት ወረዳ ደጀና ቂርቆስ ቤተክርስቲያን ተካሂዷል። በዚህ ሥነሥርዓት ላይም በብዙ ሺህ የሚቆጠር የወልቃይት እና ጠገዴ ሕዝብ የተገኘ ሲሆን የአማራን ባህል መሠረት ያደረገ የቀብር ሥነሥርዓት በደማቅ ሁኔታ ተካሂዷል።

በዚህ ወቅትም በግፍ ለተገደሉና እንደ አልባሌ ዕቃ በየቦታው ተጥለው የነበሩት የአለምሸት ልጃለም እና አዲሰይ ልጃለም አፅም ከወደቀበት ተነስቶ በክብር እንዲያርፍ ተደርጓል።

በአጠቃላይ ያነጋገርናቸው የአካባቢው ተወላጆችም ሆኑ ልዩ ልዩ ሰነዶች እንደሚያሳዩት ሕወሓት በወልቃይት ሕዝብ ላይ የፈፀመው ጅምላ ጭፍጨፋ ዋነኛ ዓላማ የአማራን ሕዝብ ከአካባቢው በማጥፋት የሥነሕዝብ አሰፋፈር ሥርዓቱን ለመቀየር ነው።

ይህ ደግሞ በአንድ በኩል አካባቢው ለም በመሆኑ ይህንን ሀብት በመዝረፍ «ታላቋ ትግራይ» የሚላትን የራሱ አገር ለመመስረት ሲሆን ከዚህ ባሻገር ወደሱዳን መውጫ ኮሪደር ለማግኘት ነው።

ይህንን እውን ለማድረግም የወልቃይትን ሕዝብ በመግፋት በምትኩ አብረዋቸው ሲታገሉ የነበሩ የትግራይ ተወላጆችን አስፍረዋል፤ የአካባቢውን ሕዝብ ማንነት በቋንቋና በሥነልቦና ለመቀየር ብዙ ጥረት አድርገዋል።

ይሁን እንጂ ማንነት በኃይል የሚቀየር ጉዳይ ላለመሆኑ የወልቃይት ሕዝብ ከአርባ ዓመት በኋላ ማንነቱን ይዞ በመቆየት እና ሕወሓትን በመፋለም ነፃ መውጣት መቻሉ ማሳያ ነው።



ዶክተር መሐመድ እድሪስ

# ሐረሪ ያሏትን ባሕሎችና ጥንታዊ ቅርሶች ወደ ኢኮኖሚያዊ ሀብትነት ሲቀየሩ እንደሚገባ ተጠቆመ

## «የሸዋል ዒድን በሐረር» መርሐ ግብር ተጠናቋል

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ሐረር፡- የሐረሪ ክልል ያሉትን ባሕሎችና ጥንታዊ ቅርሶች ወደ ኢኮኖሚያዊ ሀብትነት ለመቀየር በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መሐመድ እድሪስ አስገነዘቡ።

«ከዒድ እስከ ዒድ ወደ ሀገር ቤት» ጥሪ አንዱ አካል የሆነውና ላለፉት ሦስት ቀናት ሲካሄድ የቆየው «የሸዋል ዒድን በሐረር» መርሐ ግብር በትናንትናው ዕለት ተጠናቋል።

የማጠቃለያ መርሐ ግብሩ ላይ ዶክተር መሐመድ እንደገለጹት፥ ሐረሪ ክልል የቱሪዝም ፍሰትን የምንጨምርባቸው እንዲሁም የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን የምናጠናክርባቸው አኩሪ ባሕሎችና ቅርሶች ባለቤት ናት። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ክልሉን እየናፈቀው እንዲመጣ የሚያስችለው የቱሪዝም መስእብ የሚሆኑ ሀብቶች አሉ። እነዚህን ሀብቶች ወደ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለመቀየር በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል።

እነዚህ ሀብቶች ወደ ኢኮኖሚያዊ ጥቅምነት ለመቀየር ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት መሠራት እንዳለበትም ጠቁመዋል።

ባሕሉንና ታሪኩን በደንብ የሚያውቅ ትውልድ እንዲፈጠር በደንብ መሥራት ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።

የአጭር ጊዜ የምሥረታ ታሪክ ያላቸው አገራት ወይም ነባር ሕዝብ ኖሯቸው ነባር ማንነት ያልገነቡ ማኅበረሰቦች ቢኖሩም ያላቸውን የአጭር ጊዜ የአገር መዋቅር ተጠቅመው ባሕላቸውን ወይም ሊፈጥሩት የሚፈልጉትን እሳቤ ወደ ሀብትነት ቀይረው ሲጠቀሙበት መመልከት ተችሏል ብለዋል።

ሐረሪ ይዛ ያቆየቻቸው ስልጣኔዎች፣ ባሕሎችና ሌሎችም መገለጫዎች አገርም ልታተርፍባቸው የሚገቡ እምቅ አቅሞች መሆናቸውም አስረድተዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በመላው ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ስለ አገራቸው በኩራት ከሚናገሯቸው ድንቅ ባሕሎችና ስልጣኔዎች ሺህ ዓመታትን የተሻገረው የሐረሪ ሕዝቦች ባህልና የስልጣኔ መገለጫ የሆኑ ቅርሶች ዋናዎቹ ናቸው።

የሸዋል ዒድን በሐረር መርሐ ግብር ከሐረሪ ሕዝብ በተጨማሪ የአጎራባች ሕዝቦችን ልዩ ውበት የታየበት ነበር ያሉት ዶክተር መሐመድ፤ ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ጥሪ ተቀብለው ከተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የመጡ የዳያስፖራው ማኅበረሰብ አባላት በዚህ መርሐ ግብር ላይ መታደማቸውና በከተማው መቆየታቸው የክልሉ ሕዝብ የሚታወቅበትን እንግዳ ተቀባይነትና ፍቅር ማስመስከሪያ ናቸው ሲሉ ገልጸዋል።

በሐረሪ ክልል አስተናጋጅነት የተከበረው የዘንድርው የሸዋል ዒድን በሐረር መርሐ ግብር ደማቅ በሆነ መልኩ መከበሩን የክልሉ መንግሥትና ሕዝብ ለባሕሉና ለጥንታዊ ስልጣኔ የሰጠው ትኩረት ማሳያ ነው ያሉ ሲሆን፤ የክልሉ መንግሥትና ሕዝብ እንዲሁም ዝግጅቱ በስኬት እንዲጠናቀቅ ሚናቸውን የተወጡ አካላትን አመስግነዋል።

ከሚያዝያ 30 ጀምሮ ለሦስት ቀናት በሐረር ከተማ በድምቀት ሲከበር የቆየው «የሸዋል ዒድን በሐረር» መርሐ ግብር ትናንት የተጠናቀቀ ሲሆን በመዝጊያ ሥነ-ሥርዓቱ የፌዴራልና የክልል መንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች፣ የአጎራባች ሕዝቦች ተወካዮች፣ የዳያስፖራው ማኅበረሰብ አባላትና ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# «ኢትዮጵያ ታምርት» የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ለማነቃቃት እንደሚያግዝ አምራቾች አስታወቁ

**ውብሸት ሰንደቁ**



አዲስ አበባ፡- «ኢትዮጵያ ታምርት» የተሰኘው ንቅናቄ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ለማነቃቃት አጋዥ መሆኑን የአምራች ኢንዱስትሪ ኃላፊዎች አስታወቁ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የአምራች ኢንዱስትሪ ኃላፊዎች እንደገለፁት፤ በአገር አቀፍ ደረጃ ሚያዝያ 29 ቀን 2014 ዓ.ም የተጀመረው ኢትዮጵያ ታምርት የተሰኘው የማኑፋክቸሪንግ ንቅናቄ ዘርፉን በመደገፍና በማነቃቃት ረገድ ሚናው የጎላ ነው።

የኮቴክስ ቴክስታይል ሥራ አስኪያጅ አቶ ድልነሳው ንብረት እንደተናገሩት፤ ንቅናቄው በኢትዮጵያ አዲስ የአምራች ኢንዱስትሪዎች አብዮት እንዲቀጣጠል አስቻይ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የገበያ ትስስር ለማሳደግና አቅማቸውን ከፍ ለማድረግ ወሳኝነቱ የጎላ ነው።

ኢንዱስትሪ ትልቁ የሚፈልገው ነገር ሰላም እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ድልነሳው፤ በዚህ ረገድ ያለፉት ጊዜያት ለኢንዱስትሪ አስቸጋሪ የሚባሉ ወቅቶች መሆናቸውን አስታውሰዋል።

በነበሩት ቀውሶች ምክንያት መንግሥት ለኢንዱስትሪው ትኩረት የሚሰጥበት ዕድል ሳያገኝ መቆየቱን በመግለጽ፤ ፋብሪካዎች እስከመዘጋት በርካቶችም ከአቅም በታች እስከማምረት መድረሳቸውን አንስተዋል።

አሁን ላይ በመንግሥት ደረጃ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ መጀመሩ የተዘጉ ኢንዱስትሪዎች እንዲከፈቱ፤ በተለያዩ ችግሮች ከአቅማቸው በታች እያመረቱ ያሉትም በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ በማገዝ ለዘርፉ ትልቅ መነቃቃትን ይፈጥራል ብለዋል።

ንቅናቄውም ይበልጥ ውጤት እንዲያመጣ መንግሥት ከትናንሽ አምራቾች ጀምሮ በየትኛውም ደረጃ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ሊያበረታታ ይገባል። በተጨማሪም የአምራች ኢንዱስትሪዎች የመሥሪያ ቦታና የኃይል አቅርቦት ችግር መፍታት ልዩ ትኩረት የሚያስፈልገው ጉዳይ መሆኑን ገልፀዋል።

የኬሬዢ ኢትዮጵያ ሌዘር ማኑፋክቸሪንግ ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ ዘላለም መርዓዊ በበኩላቸው ድርጅታቸው ደረጃቸውን የጠበቁ የቆዳ ምርቶችን ወደ ተለያዩ የዓለም አገራት በመላክ ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠሩን ገልጸው፤ መንግሥት የጀመረው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ዘርፉን ይበልጥ ገበያቸውን እንደሚያነቃቃ ዕምነታቸው መሆኑን ጠቁመዋል።

ከዚህ በፊት ይታዩ የነበሩ ችግሮች በንቅናቄው ከተፈቱ የኢትዮጵያን የማኑፋክቸሪንግ አብዮት ማቀጣጠል ይቻላል ብለዋል።

በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ይበልጥ እንዲሳካ ተኪ ምርቶችን የመጠቀም ባህሉ ሊስፋፋ ይገባል፤ በተለይም የመንግሥት ተቋማት ከውጭ ምርቶች ይልቅ የአገር ውስጥ ምርቶችን ሊጠቀሙ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ኬሬዥ ኢትዮጵያ ሌዘር ማኑፋክቸሪንግ ኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ በሌሎች የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ልዩ ልዩ ተቋማት ፍላጎት ከውጭ የሚገቡ የቆዳ ውጤቶችን በአገር ውስጥ በሚመረቱ ምርቶች እየተካ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ይህ ልምድ በየዘርፉ በማስፋት ከአገር ውጪ ግዢያቸውን የሚፈፅሙ ተቋማት በቋሚነት ፊታቸውን ወደአገር ውስጥ ምርቶች እንዲያዞሩ በማድረግ አምራች ዘርፉን ማሳደግ ይቻላል ብለዋል።

እንደ አቶ ዘላለም ገለጻ፤ በንቅናቄው ማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ላይ ሥር የሰደዱ ችግሮች መፍትሄ ለማበጀት የሚያግዙ ሃሳቦች ለማሰባሰብ ይረዳል። በተለይ ለፖሊሲና በመሰል አሠራር ሥርዓቶች ግብዓት የሚሆኑ ጠቃሚ መረጃዎችም ለማግኘት ተመሳሳይ መርሃግብሮች ወሳኝነት አላቸው።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን ከማጠናከር ጎን ለጎን በአምራቹ ዘርፍ ላይ የተጋረጡ የኃይል አቅርቦት፣ የመሠረተ ልማት፣ የውጭ ምንዛሬና የመሥሪያ ቦታ ችግሮችን መቅረፍ ያስፈልጋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከዚህ ባለፈ ለውጭ ኢንቨስተሮች የሚደረጉ ማበረታቻዎችን ለአገር ውስጥ አምራቾችም በመስጠት ኢንዱስትሪዎች በቂ የፋይናንስ አቅርቦቶች ማመቻቸት ያስፈልጋል ብለዋል።

# «አገርን ለማስቀጠል አስተሳሰባችንን በበጎነት መቃኘትና የቀደምት የእምነት አባቶችን ፈለግ መከተል አለብን»

\- የሃይማኖት አባቶች



አዲስ አበባ፡- አገርን እንደ አገር ለማስቀጠል አስተሳሰባችንን በበጎነት መቃኘትና ፍቅርንና ሰላምን በመስበክ የቀደምት የእምነት አባቶችን ፈለግ መከተል አለብን ሲሉ የሃይማኖት አባቶች አሳሰቡ።

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ከፍተኛ አመራሮች ከጎንደር ከተማ የእምነት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች ጋር ትናንት የጋራ ምክክርና ውይይት አካሂደዋል።

የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሀጂ ኡመር እድሪስ በመድረኩ እንዳሉት፤ የእስልምና እና የክርስትና ሃይማኖቶች ለብዙ ሺህ አመታት አብረው በጋራ የኖሩና የእምነቶቹ ተከታዮችም የጋራ የአብሮነት እሴቶች የገነቡ ታላላቅ ሃይማኖቶች ናቸው።

የሰው ልጅ የሃይማኖት እምነት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያለ እና የነበረ ወደፊትም የሚኖር መሆኑን ጠቅሰው፤ ሰላም ለሰው ልጆች የህልውና መሠረት በመሆኑ ሁሉም ሃይማኖቶች ለሰላም በአንድነት እንዲቆሙ አሳስበዋል።

«በጎንደር በተፈጠረው ችግር አዝኛለሁ ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ነገር ግን ከመጣሁ በኋላ በውይይት መድረኩ የሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታዮች ያሳዩት የአብሮነት፣ የመከባበርና ወንድማማችነት ስሜት ከልብ አስደስቶኛል» ብለዋል።

የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ከኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጋር በመቀናጀት በግጭቱ የተጎዱ ወገኖችን በመደገፍና የፈረሱ ተቋማትን መልሶ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት አብሮ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል።

«በጎንደር ከተማ በሃይማኖት ሽፋን የተፈጠረው ችግር የከተማዋን ታሪካዊነት የማይመጥንና በሰዎች ሕይወትና ንብረት ላይም የደረሰው ጉዳትና ጥፋት አሳዛኝ ነው'» ያሉት ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ብጹዕ አቡነ ዮሴፍ ናቸው።

«አገርን እንደ አገር ለማስቀጠል አስተሳሰባችንን በበጎነት መቃኘት አለብን» ያሉት አቡነ ዮሴፍ፤ የሰላም ባለቤት ፈጣሪ ቢሆንም እኛ የሰው ልጆች በምናደርገው በጎ ነገር ሰላምን ማረጋገጥ እንችላለን ሲሉ ገልፀዋል።

«ለልጆቻችን በጎና አስተማሪ የሆነ መልካም ነገር ትተን ማለፍ የምንችለው እኛ ወደ ልባችንና ወደ ቀልባችን ስንመለስ ነው» ያሉት ዋና ፀሐፊው፤ በሃይማኖት ስም የሚነግዱትን በጋራ ተዉ ብለን መገሰጽና መምከር አለብን ብለዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻዲቁ አብዶ በበኩላቸው ሁላችንም ከሰላም እንጂ ከግጭት ተጠቃሚ መሆን እንደማንችል መገንዘብ አለብን ብለዋል።

ብሔርም ሆነ ሃይማኖት ዛሬ አልተፈጠሩም ያሉት ፓስተር ጻዲቁ፤ አገራችንን የሰላም፣ የፍቅርና የመከባበር ምሳሌ በማድረግ አንዱ የሌላውን የእምነት ተቋም በመገንባት አብሮነትን በተግባር ልናሳይ ይገባል ሲሉ መግለፃቸውን የኢዜአ ዘገባ ያመለክታል።

ተሳታፊዎቹ በውይይቱ ማጠቃለያ የሁለቱን እምነቶች አብሮነት የሚያጠናክሩና ችግሩን በዘላቂነትና በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ባለ 5 ነጥብ የአቋም መግለጫ በማውጣት አጠናቀዋል።

ዜና

# ተቋሙ የመረጃ ደኅንነትን ለማረጋገጥ ሶፍትዌሮችን እንዲያበለጽግ ተጠየቀ



አዲስ አበባ፡- የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደር /ኢመደአ/ የመረጃ ደኅንነትን ለማረጋገጥ ሶፍትዌሮችን እንዲያበለጽግ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ።

ቋሚ ኮሚቴው ማሳሰቢያውን የሰጠው ሰሞኑን በአስተዳደሩ ተገኝቶ የ9 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በገመገመበት ወቅት ነው።

ኢንፎርሜሽን በየትኛውም ዘርፍ ወሳኝ ግብዓት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ተቋሙ የኢንፎርሜሽን እና የኢንፎርሜሽን መሠረተ-ልማት ደኅንነት በማረጋገጥ ረገድ የሚሠራቸውን ሶፍትዌሮችን የማልማት ሥራ ኮሚቴው በበጎ ጎኑ ተመልክቷል።

በሳይበር ዘርፍ ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎች በተቋሙ ተገኝተው ባላቸው ተሰጥዖ መሠረት የተለያዩ ሶፍትዌሮችን እንዲያበለጽጉ የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥልም ቋሚ ኮሚቴው አስገንዝቧል።

የሳይበር ጥቃቶችን መከላከል እና የአገር ሉዓላዊነትን መጠበቅ የዚህ ተቋም ኃላፊነት ብቻ ባለመሆኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት እንደሚያስፈልግ ቋሚ ኮሚቴው አመላክቷል።

ተቋሙ ሐሰተኛ መረጃዎችን በማጋለጥ እና የአገርን ሉዓላዊነት ከማስጠበቅ ረገድ ያበረከተው አስተዋጽኦ ቀላል እንዳልሆነ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ዲማ ነገዎ (ዶ/ር) ጠቁመው፣ በተለያዩ ጊዜያት በአገራችን የሚደረጉ የጥቃት ሙከራዎች በተቋሙ መምከናቸውንም ከሪፖርቱ መረዳት ይቻላል ብለዋል።

የኢመደአ ዋና ዳይሬክተር ሹመቴ ግዛው (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ ተቋሙ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖን መቋቋም እንዲቻል በቴክኖሎጂ የታገዘ ጥቃትን ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ ሶፍትዌሮችን ማበልጸግ መቻሉን ገልጸዋል።

ደኅንነታቸው የተጠበቀ ምርት እና አገልግሎቶችን በከፊል እና በሙሉ ዓቅም በማበልጸግ እና የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን የማረጋገጥ ሥራዎች መሠራታቸውንም ተናግረዋል።

የኢንፎርሜሽን እና የኢንፎርሜሽን መሠረተ-ልማት ደኅንነትን የማስጠበቅ ዓቅም በመገንባት፣ የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅሞች ከማስጠበቅ ረገድ፣ ቁልፍ ተግባራት እንደተከናወኑ ዋና ዳይሬክተሩ አስረድተዋል።

ዘርፉ ተለዋዋጭ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በታሰበው ፍጥነት መጓዝ እንዲቻል የሳይበር ደኅንነት የሕግ ማዕቀፎች እና የጥራት ደረጃዎች እንዲወጡ እና በፍጥነት እንዲጸድቁም፣ ምክር ቤቱ አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል እንዲያደርግላቸው ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘው መጠየቃቸውን ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።



# በቀጣይ አሥር ዓመታት የዓሣ ምርትን 260 ሺህ ቶን ለማድረስ እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ

ጸጋዬ ጥላሁን

አዲስ አበባ፡- በአሥር ዓመቱ ስትራቴጂክ እቅድ በግሉ ዘርፍና በመንግሥት ተሳትፎ ከዓሣ ሀብት ልማት 260 ሺህ ቶን የሚጠጋ ምርት ለማግኘት እየተሠራ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ገለፀ።

ኢንስቲትዩቱ በዓሣ ሀብት አጠቃቀም ወቅታዊ ሁኔታ፣ ተግዳሮቶች፣ መልካም ዕድሎችና ቀጣይ አቅጣጫዎችን በተመለከተ ትናንት ባካሄደው ውይይት እንደተገለጸው፤ በቀጣይ አሥር ዓመታት የዓሣ ምርትን አሁን እየተመረተ ካለበት 60 ሺህ ቶን ወደ 260 ሺህ ቶን ለማድረስ እየተሠራ ይገኛል።

በግብርና ሚኒስቴር የዓሣ ሀብት ልማት ዳይሬክተር አቶ ሁሴን አበጋዝ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በዓመት ከ94 ሺህ በላይ ቶን የማምረት አቅም ቢኖራትም አሁን እያመረተች ያለችው 60 ሺህ ቶን ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ለዓሣ ግብርና ልማት ምቹ ሁኔታዎች አላት ያሉት አቶ ሁሴን፤ ዘርፉ በአግባቡ እየተሠራበት አይደለም፣ ዋና ዋና ግብአቶች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

የግብአት እጥረት፣ የአጠቃቀም ክፍተት፣ የግንዛቤ እና በሌሎች ችግሮች ምክንያት በዘርፉ አጥጋቢ ውጤት ማምጣት አልተቻለም። በቂ ምርት አምርቶ ለተጠቃሚው ማቅረብም አዳጋች ሆኗል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደርሳቸው ገለፃ በአሥር አመቱ ስትራቴጂክ እቅዱ በግሉ ዘርፍ እና በመንግሥት ተሳትፎ ምርቱ ወደ 260 ሺህ ቶን ለማድረስ ይሠራል።

የዓሣ ሀብትን ትኩረት ሰጥቶ ማልማት ተጨማሪ ምግብ ከማግኘት ባሻገር፣ በሥነ-ምግብ ይዘቱ የተሻሉ ከሚባሉት የእንስሳት ተዋጽኦዎች አንዱ በመሆኑ አገሪቱ ያሉባትን የአመጋገብ ሥርዓት ክፍተቶችን ለማሻሻል ከፍተኛ ጠቃሜታ እንዳለው ጠቁመዋል።

በውይይቱ የሰበታ ብሔራዊ ዓሣና የውሃ ውስጥ ሕይወት ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር ዶክተር አስቻለው ላቀው በበኩላቸው እንደገለፁት፤ እየተገነቡ ያሉ አዳዲስ ግድቦች አዲስ የውሃ አካላትን እየፈጠሩ በመሆኑ ለዓሣ እርባታ ምቹ ሁኔታን እየፈጠሩ ናቸው።

የዓሣ ምርትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና የአመጋገብ ሥርዓትን ለመቀየር ዓይነተኛ ሚና እንዳለው ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅት ዓሣ አስጋሪዎች ከሀብቱ የሚያገኙት ገቢ ዝቅተኛ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር አስቻለው፤ ያሉትን የውሃ አካላት በዘላቂነት ጥቅም እንዲሰጡ በማድረግና መስኩን በማዘመን ከሀብቱ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ አገሪቱ የእንስሳትና የዓሣ ሀብትን ከመጠቀም አኳያ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እያገኘች አይደለም። ይህን ለመቀየርና አጥጋቢ ውጤት ለማምጣት በመስኩ ያሉ ችግሮች ተለይተው እልባት ሊያገኙ ይገባል።

ከአመጋገብ ሥርዓት መሻሻል ባለፈም የ2030 በዓለም የዘላቂ ልማት ግብ በምግብና በስነ ምግብ ራስን ለመቻል የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት እንደሚያግዝም አመልክተዋል።

የዓሣ አመራረትና አያያዙ ዝቅተኛ መሆናቸውን፣ የምርምር ውጤቶችን ተደራሽ ለማድረግ ቢሞከርም ትግበራው በቂ አለመሆኑን የፓናሉ ተወያዮች አስረድተዋል።

በግብርና ሚኒስቴር የግድብ መሐንዲስ የሆኑት ኢንጂነር ያሬድ ሙላት ተፈጥሮ ብዙ ነገሮችን ብትለግስም የዓሣ ሀብት ልማት ዝቅተኛ ነው። የግድብ ፕሮጀክቶች ሲቀረፁ ለዓሣ ሀብት ልማት ግምት ውስጥ ያስገባ በቂ እቅድ አለመኖር፣ የትኩረት ማነስ፣ የዲዛይን፣ የግንባታ ችግሮችና ሌሎች ምክንያቶች ከመስኩ የሚጠበቀውን ውጤት ማግኘት እንዳላስቻለም ጠቁመዋል።

በመስኖ ግድቦችና በሌሎች የውሃ ፕሮጀክቶች ለዓሣ ሀብት የሚውለው ወጪ አነስተኛ ቢሆንም ትኩረት አይሰጥም። ለወደፊቱ ግድቦች በሚገነቡበት ወቅት በቂ ዝግጅት ማድረግና ትኩረት እንዲሰጠው ማድረግ ይገባል ብለዋል።

# “በመሠረታዊ ሸቀጦች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ይኸ ዕድገት ከአምናው ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ ጭማሬ አለው። ለዚህ ዕድገት መመዝገብ በዋነኝነት በግብርናው ዘርፍ በተለይም በሰብል ምርት ላይ የታየው እመርታ ተጠቃሽ መሆኑን አብራርቷል።

የመኸር ምርት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የበጋ ስንዴን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከፍተኛ ርብርብ መደረጉን ተከትሎ 613 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ከ25 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚሰበሰብ እንደሚጠበቅ መግለጫው አመልክቶ፤ ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተጽዕኖ ቀስ በቀስ እያገገመ የሚገኘው የአገልግሎት ዘርፉ ላይ ተስፋ ሰጪ ዕድገት እየታየ ነው። በተመሳሳይ መጠነኛ የዕድገት መቀነስ የተመዘገበበት የኢንዱስትሪው ዘርፍ እንደገና እንዲያንሠራራ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ይገኛል። በጦርነቱ ተቀዛቅዞ የቆየውን የአገር ውስጥና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ድርሻ ለማሳደግ የተደረጉ ርብርቦች ውጤት ማምጣት ጀምረዋል ሲል አብራርቷል።

የሥራ አጥነት ለመቀነስ በተሠሩ ሥራዎችም ባለፉት 9 ወራት ውስጥ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ገደማ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የጠቀሰው መግለጫው፤ ከዚህ ውስጥ የአገር ውስጥ የተፈጠረው የሥራ ዕድል ሰፊውን ቁጥር ቢሸፍንም፣ ሞያዊ ሥልጠና ወስደው በውጭ አገራት ማለትም በኳታር፣ በዮርዳኖስና በተባበሩት የዓረብ ኤምሬቶች የሥራ ዕድል የተመቻቸላቸው ዜጎች ቁጥር ቀላል የሚባል አለመሆኑን ገልጿል።

በቀጣይ ጊዜያት በኢኮኖሚያችን ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጫናዎችን ለመቀነስ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ መሆኑን መግለጫው አመልክቶ፤ መሠረታዊነታቸው የታመነባቸው እንደ ስንዴ፣ ዘይት፣ የሕፃናት ምግብ እና ስኳር የመሳሰሉ የፍጆታ ዕቃዎች አስመጪዎች በፍራንኮ ቫሉታ አሠራር የራሳቸውን የውጭ ምንዛሪ በመጠቀም እንዲያስገቡ ፍቃድ ተሰጥቷቸዋል። የመድኃኒት፣ ነዳጅ፣ ማዳበሪያ፣ ዘይት፣ እና ሌሎችም መሠረታዊ ሸቀጦች ግዥን በተገቢው ሁኔታ እንዲካሄድ፣ በእነዚህ ሸቀጦች አቅርቦት ላይ መንዛዛት እንዳይኖር በግዥ ሥርዓቱ ላይ አስፈላጊው ማስተካከያ ይወሰዳል ብሏል።

ከዚህ በተጨማሪ ከአንዳንድ አስመጪዎች ጋር በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል በተደረገ ውል አሁን ላይ መክፈል ሳያስፈልግ በ“deferred letter of credit” አማካይነት እንደ ዘይት፣ ስንዴ እና ስኳር ያሉ መሠረታዊ ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ እየተመቻቸ እንደሚገኝ ጠቅሶ፤ ነዳጅን በተመለከተ የዋጋ ንረቱን ተከትሎ የሚኖረውን የበጀት ጫና መቀነስ ይቻል ዘንድ፣ ወጥ ከሆነው የመንግሥት የነዳጅ ድጎማ ቀስ በቀስ በመውጣት በተጠና መንገድ ድጎማው ለሚያስፈልጋቸው አካላት ብቻ እንዲሆን በዕቅድ እየተሠራ መሆኑን አስታውቋል።

በበጋ ስንዴ ምርት ላይ የታየውን አበረታች ውጤት በማጎልበት፣ የስንዴ ምርትን ሙሉ በሙሉ ከውጭ ማስገባት ለማስቀረት የሚደረገው ርብርብ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አረጋግጦ፤ የምርቱ መጨመር በራሱ ገበያውን ለማረጋጋት ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል ሲል ምክር ቤቱ በመግለጫው አስረድቷል።

# «ወራሪው ቡድን ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሞት የሽረት ትግል ላይ ናቸው። ወራሪው ኃይል ካለው ጥፋት አልማር ብሎ ለዳግም ጥፋት እየተዘጋጀ ነው ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ ሁሉንም የሰላም አማራጮችን በመዝጋትና ለጠላት ተልዕኮዎች በመገዛት ለሚፈጸሙ ትንኮሳዎችና ወረራዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ የማያዳግም ዕርምጃ እንደሚወስድ ሁሉም ወገን ሊገነዘበው ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

«ጦርነት ምርጫችን አይደለም፤ ለማንም አይበጅም» ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የሁልጊዜ ቅድሚያ ምርጫው ሰላማዊ መፍትሄ ነው። የሰላም መንገድ የሕዝቡን ጥያቄዎች በዘላቂነት የሚፈታ እስከሆነ ድረስ ሰላም ከሁሉም መንገዶች የላቀው ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት፣ የአማራ ልዩ ኃይል፣ ፋኖ፣ የአፋር ልዩ ኃይል እንዲሁም የሁሉም ክልሎች የጸጥታ ኃይሎች የጥፋት ቡድኑን እኩይ ዓላማ በማክሸፍ ረገድ በኢትዮጵያ ታሪክ የማይረሳ ገድል ፈጽመዋል ሲሉ ተናግረዋል።

መላው ኢትዮጵያውያንና በውጭ አገራት የሚኖረው ዳያስፖራ ለጸጥታ ኃይሉ ደጀን በመሆን ዓለምን ያስደነቀ ተግባር ፈጽመዋል፤ ይህንንም በየጊዜው አስመስክረዋል ብለዋል።

በመላው ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የአገራቸውን ዕውነትና ሀቅ ለዓለም ለማሳወቅ ላደረጉት ርብርብና ላስገኙት ውጤት ምስጋና አቅርበዋል።

ኢትዮጵያን ለማጽናት ሲሉ በሕግ ማስከበርና በህልውና ዘመቻ መስዋዕትነት ለከፈሉት ዜጎች ኢትዮጵያ ልዩ ክብር አላት ብለዋል።

በህልውናው ዘመቻና በሕግ ማስከበር ዘመቻ ከፍተኛ ሚና ለተጫወቱት ለወታደራዊና ለሲቪል አመራሮች የተሰጠው ዕውቅናና ሽልማት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የአገር ፍቅር ተምሳሌት ሆኖ ሲታወስ የሚኖር ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በአንጻሩ ለጥፋት የተዘጋጁት ሕወሓትና ሌሎች ፅንፈኛ ኃይሎች በሚፈጽሙት ጥቃት ሚሊዮኖች ከቀዬያቸው መፈናቀላቸውን የጠቆሙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በርካቶች ደግሞ ለስነልቦና ቀውስ መዳረጋቸውን ገልጸዋል።

በሕግ ማስከበርና በህልውና ዘመቻ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት ኢትዮጵያውያን ተፈናቃይ ወገኖቻቸውን ለማቋቋም በሚደረገው ጥረትም የበኩላቸውን እንዲወጡ ጠይቀዋል።

የአማራ ክልል ባዘጋጀው መርሐ ግብር ላይ ለአንድ ሺህ 471 የክልሉ ጸጥታ አካላት የማዕረግ ዕድገት እንዲሁም በእርከን፣ በሜዳሊያና በምስክር ወረቀት የተሸለሙትን ጨምሮ በድምሩ ለሁለት ሺህ 197 አባላትና አመራሮች ዕውቅናና ማበረታቻ ተደርጓል።

ከዚህ ባለፈም በህልውና ዘመቻው በቡድን (በክፍል) ደረጃ ጀብዱ በመፈፀም የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ለመከላከያ ሰራዊት ሦስት ክፍለጦሮችና 12 ሻለቃ የዓይነት ሽልማት፣ ዕውቅና ተሰጥቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ቀጣይነት ያለውና የተጠናከረ ሊሆን ይገባል !

ኢትዮጵያ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የመስጠት የቆየ ባህል ያላት ሀገር ናት። ዜጎች በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ምክንያት ጉዳት ሲያጋጥማቸው ሰዎች በግል ወይም በቡድን ሆነው ችግር የደረሰበትን ማኅበረሰብ በጉልበት፣ በገንዘብ እንዲሁም ጊዜያቸውን ሰውተው ይደግፋሉ። ይሄ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዜጎች በፍጹም ወንድማማችነት ችግራቸውን በጋራ እና በመደጋገፍ የሚወጡበት ሲሆን ምላሹም ምስጋናና ምርቃት ብቻ ነው።

ይሁን እንጂ የበጎ አድራጎት ስራ በተጠናከረና በተደራጀ መልኩ በተቋማት ተደግፎና ቀጣይነት ኖሮት አይከናወንም ነበር። በመሆኑም አንድ ጊዜ ብልጭ፤ ሌላ ጊዜ ከስም እያለ ቆይቷል። ሆኖም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ግን ስራው ትኩረት ተሰጥቶት መንግሥታዊ አስተባባሪ ተቋም ተቋቁሞለት ጭምር ወደ ሥራ ገብቷል። የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም፣ የተማሪዎች አልባሳት ድጋፍ፣ የአረጋውያንን ቤት ማደስ ፣ ማዕድ ማጋራት፣ ተፈናቃዮችን መደገፍ እና የወደሙ ተቋማትን መልሶ የማቋቋም ሥራ በተቆራረጠ መልኩም ቢሆን የታዩና የሚያስመሰግኑ በጎ ተግባራት ናቸው። ሆኖም ግን የበጎ አድራጎቱ ስራ በሚፈለገው መልኩ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተጠናክሮ ቀጥሏል ለማለት አያስደፍርም። አንዳንድ ቦታዎች እና ስራዎች ላይ ደግሞ የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ሲሰሩ የሚሰራ፤ ለቀቅ ሲያደርጉት ደግሞ የሚዘነጋ እየሆነም ነው። ያም ሆኖ ግን ዛሬም ድረስ የበጎ አድራጎት ስራዎች በተለያየ መልኩ ተግባራዊ መደረጋቸው ቀጥሏል።

ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚደረገውን ዓመታዊ የቤት እድሳት መርሀ ግብር ክረምቱ ከመግባቱ በፊት አስጀምረዋል። የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ገንዘብና ጉልበት የሌላቸውን ዜጎች መደገፍ በመሆኑ በመርሀ ግብሩ ላይ ግለሰቦች፣ የንግድ እና የመንግሥት ተቋማት በአካባቢያችን ላሉ በርካታ ሰዎች ምቹ እና ሰብአዊ ክብርን መሠረት ያደረገ ድጋፍ እንዲያደርጉ አሳስበዋል።

በተለይም የንግድ ድርጅቶች ማኅበራዊ ኃላፊነትን እንዲወጡም ጥሪ አድርገዋል። ይህንን ተከትሎ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመጪው የክረምት ወራት ከሦስት ሺህ በላይ ቤቶችን ለማደስ ዕቅድ አውጥቶ ወደስራ ገብቷል፤ ሌሎች ክልሎችም ይሄንኑ ጥሪ መነሻ አድርገው መልካም ፈቃደኛነታቸውን እያሳዩ ነው። ይሄ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበትና ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ነው።

የበጎ አድራጎት ስራ የሀገር መሪ ሲጀምረው የሚሰራ ፊቱን ወደሌሎች ሥራዎች ሲያዞር ደግሞ የምናቆመው መሆን የለበትም። በጎ አድራጊዎችም ሆኑ አቅመ ደካሞቹ አብረው የሚኖሩ ጠዋት ማታ የሚተያዩ የማህበረሰበ ክፍሎች ናቸው። ስለዚህ ወቅትን ጠብቆ ወይም መሪን ተከትሎ ለታይታ ብቻ የበጎ አድራጎት ስራ ላይ መሰማራት ተገቢ አይሆንም። ስለዚህ ሁልጊዜም ስራው ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆን አለበት።

አሁን በሀገራችን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በሚሊየን የሚቆጠሩ ዜጎች በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያት ተፈናቅለው እስካሁን ድረስ ጸሀይና ንፋስ ሲፈራረቅባቸው ቆይቷል፤ በቀጣይ ደግሞ ክረምቱ ገብቶ ለዝናብና ብርድ ከመዳረጋቸው በፊት መልሶ በማቋቋም፣ ቤታቸውን ገንብቶ የቀድሞ ኑሯቸውን እንዲኖሩ ማድረግ ይገባል። ሀገር የሚቆመው በጥቂቶች ሳይሆን በህዝቦች ህብረትና መተሳሰብ ጭምር ነው።

በመሆኑም ከመንግሥት ባሻገር ለዜጎቻችን ልናስብላቸውና ልንደግፋቸው ይገባል። አቅመ ደካሞችን መደገፍ ለተደረገለት ሰው ትልቅ ድጋፍ ሲሆን፤ ለአድራጊው ደግሞ የህሊና እርካታ የሚሰጥ ነው። በሰለጠነው ዓለም የምናየውም ይሄንኑ ነው ።አንድ ሰው ሙሉ ነው የሚባለው፣ ለተሻለ ስራና ስልጣን የሚታጨው በሰራው የበጎ ፈቃድ ስራዎች ተመዝኖ ነው።

የበጎ ፈቃደኞች ሌላው ተግባር የኢኮኖሚ አቅማቸው የተሻሉ የሚባሉ ሰዎችን ቀና ለሆኑ ተግባራት ማነሳሳት ጭምር ነው። በጎ ፈቃደኞች ከፍተኛ ዋጋ ያለው የማኅበራዊ ግንኙነት ልምድ ያላቸው እና ብዙውን ጊዜ በመረጡት የሥራ መስክ ውስጥ ካሉ ከማንኛውም አካላት የተሻሉ ናቸው፡፡ በጎ ፈቃደኝነት በማኅበራዊ መስክ ውስጥ ሥራውን በሚሠሩ የመንግሥት እና የሕዝብ መዋቅር እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ ዝግጁ የሆኑ መሪዎችን ለማቋቋም አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም በሀገራችን በተለያየ ቦታና መልኩ ለሚካሄደው የክረምት የበጎ አድራጎት ተግባር በጎ ምላሽ በመስጠት ልንተባበር ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በ"ስለ ኢትዮጵያ" - ስለኢትዮጵያችን ትናንት፣ ዛሬ እና ነገ

በየኔነው ስሻው

አገር በትናንት ተግባራችን ዛሬ የደረሰች፤ በዛሬ ኑረታችን ፍሬ ለነገ የምትሻገር፤ በሕልምና ትልማችን ልክ ለነገው ትውልድ የምንሰራት ናት። የትናንት መሪዎችና ሕዝቦች የዛሬዋን አገር በሕልማቸው ሰርተው እንዳስረከቡን፤ የነገዋን ታላቅ አገር ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ አጽንቶና ሰርቶ ማሻገር ደግሞ ከዛሬው የእኛው ትውልድ የሚጠበቅ የቤት ስራ ነው። ይህ የሚሆነው ግን የትናንቷ ኢትዮጵያ እና ቀደምቶቹ ኢትዮጵያውያን በትናንት መስታወትነት ሲፈተሹ፤ የአሁኑ ባላደራዎችም በዛሬ ምግባርና ሕልማቸው ሲመዘኑ፤ የሁለቱ ድምር ውጤትም ስለ ነገዋ ታላቅ አገርና ስለመጪው ትውልድ የሚፈጥረውን የጠራ የብልጽግና መስመርና ከፍታ በሚኖረው ሕልም ልክ ሲፈተሽ ነው።

ሰሞኑን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በጅግጅጋ ከተማ አንድ ታላቅ መርሃ ግብር እያከናወነ ይገኛል። ይህ መርሃ ግብር "ስለ ኢትዮጵያ" የተሰኘ ሲሆን፤ በመርሃ ግብሩ የፎቶ አውደ ርዕይ፣ የመጽሐፍ ምርቃት እንዲሁም በኢትዮጵያ አሁናዊ ፈተናዎችና መልካም እድሎች ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይት የተካሄደበት ነበር። የእነዚህ ሶስት ሁነቶች ግብም ኢትዮጵያን በትናንት ኑረቷ፣ በዛሬ እውነቷ እና በነገ ተስፋዎቿ ላይ ሰፊ ውይይትና ምልከታ በማድረግ ግንዛቤን ማስጨበጥ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያሏቸው ጥያቄዎች፣ እንዲሁም የመሪዎቻቸው እሳቤና ምላሽ ትናንት ምን ነበር? ዛሬ ላይስ እንዴት ይገለጻል? ነገ እንዲሆን ከሚጠበቀው አኳያ ምን ሊከወን ይገባል? የሚሉ ሁነቶች ላይ ያተኮረም ነው።

ይሄን በተመለከተ ከውይይቱ መድረክ ባለፈ በተለይ የፎቶግራፍ አውደ ርዕዩንና የፎቶ መጽሐፉን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ እንዳመለከቱት፤ የፎቶ ግራፍ አውደ ርዕዩ በየዘመኑ የነበሩ መሪዎች ምን ርዕይ ነበራቸው? በየዘመናቱ የተነሱ የሕዝብ ጥያቄዎች ምን ነበሩ? እንዴትስ ተመለሱ? አገዛዞቹስ የሕዝቡን ጥያቄዎች በመመለስ ረገድ ምን ተሳካላቸው? ምንስ አልተሳካላቸውም? የሚለውን የሚያሳይ ነው። በድርጅቱ ተዘጋጅቶ የተመረቀው ስለኢትዮጵያ የፎቶ መጽሐፍም በዋናነት ያካተተው በንጉሱ፣ በደርግና በኢህአዴግ ዘመን የነበረውን ሀገራዊ ህልም፣ የሕዝብ ጥያቄና የስርዓት ለውጥ ሲሆን፤ ከሀገራዊ ለውጡ ጋር በተያያዘም ስለ ኢትዮጵያ ፈተና፣ ድልና ተስፋ የሚያመላክት ነው።

በኢፕድ የተዘጋጀው ይሄን አይነት መርሃ ግብር ዛሬ አገር ይዞ ያለው ሕዝብም ሆነ አገር እየመራ ያለው መሪ (ስርዓቱ እንደ አጠቃላይ)፤ ስለ ትናንት የሕዝብ አስተዳደርና ጥያቄዎች እንዲሁም ለጥያቄዎቹ ይሰጡ የነበሩ ምላሾች እንዲገነዘብ እድል የሚሰጥ ነው። ይህ ሲባል በወቅቱ የነበረው ሥርዓት የነበረውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምልከታ፤ የሕዝቡ እና የሥርዓቶቹን ቁርኝት፤ ሕዝቡ በየሥርዓቶቹ ሲያነሳቸው የነበሩ ሁሉን አቀፍ ጥያቄዎች ይዘትና ትኩረት፤ ብሎም የየዘመናቱ ሥርዓት መሪዎች የህዝብን ጥያቄ ተቀብለው የሚያስተናግዱበትን (በመልካምም በመጥፎም የሚነሱ ሊሆኑ ይችላሉ) አግባብ እንዲያውቅ የሚያስችሉ ናቸው። ይህ ሲሆን ደግሞ የትናንቶቹ ሥርዓቶችና አመራሮች ከሕዝባቸው ጋር ያላቸውን አዎንታዊም አሉታዊም ቁርኝት ከመገንዘብ ባለፈ፤ ዛሬውን እንዲፈትሽና ነገውን በወጉ እንዲተልም መንገድ አመላካቾችም ሆነው ያገለግላሉ። ምክንያቱም የትናንት መልካም ግንኙነቶች ለዛሬው መሰረት የሚጥሉ እንደሆኑት ሁሉ፤ ያልተገቡ ሂደቶችን በመለየት ዛሬ ላይ ታርመው የተሻለ ስልትና መንገድ ለመያዝ ትምህርት ስለሚሰጡ ነው። ይህ ግን ሁሉም እንዳለ ይወሰዳል ወይም ይጣላል ማለት አይደለም። ምክንያቱም ትናንት የነበረው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁነት ከዛሬው ጋር የሚወራረሰውም፣ የሚያለያየውም አያሌ እውነቶች አሉ። በመሆኑም የትናንቱን መልካምም ሆነ መልካም ያልሆነ ሂደት ለዛሬ ትምህርት የማድረጉ ጉዳይ እንደየዘመኑ እውነትና ተጨባጭ ሁኔታ እየተመዘነ የሚወሰድ መሆኑ ሊታወቅ የሚገባው ነው።

ይህ ሲባል የትናንቱ አገራዊና ዓለማቀፋዊ ሁኔታ ከዛሬው ጋር ሊገናዘብ ያስፈልጋል። የትናንቱ የሕዝብ ፍላጎትና ትያቄ ከዛሬው የሕዝብ ፍላጎትና ጥያቄ ጋር ሲነጻጸር አገራዊ ገጹም የቴክኖሎጂ እድገቱም ጋር ተገናዝቦ መሆን ይጠበቅበታል። ለምሳሌ፣ የትናንቱ የመደብ፣ የመሬት ላራሹና የብሔር ጥያቄ እና የነበረው ምላሽ ዛሬ ላይ በትናንቱ ቅርጽና ይዘት አይቀርብም። ምናልባት ዛሬ ላይ ከፍ ብሎ የሚነሱት እኩል የመልማትና ተጠቃሚነትና፣ ሰላምና ዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደርና መሰል ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ የዛሬ ጥያቄዎች ደግሞ ሚዛናቸው ይለያይ እንጂ ትናንትም ሲጠየቁ የነበሩ ናቸው።

ለምሳሌ፣ ዛሬ ላይ ከፍ ብሎ የሚነሳው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት ጉዳይ፤ ትናንት በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥትም የሚነሳ፤ በደርግ ስርዓትም ሆነ በኢህአዴግ ወቅት የሚስተጋባ ነበር። ጥያቄውም እንደየሥርዓቶቹ መልክና አተያይ ሲመለሱ መቆየታቸውም እሙን ነው። ታዲያ በየሥርዓቱ ጥያቄዎቹ እንዴት ተነሱ፤ እንዴትስ ሥርዓቶቹ አራማጆች ምላሽ ተሰጣቸው፤ የሕዝቡስ እርካታ ምን ነበር፤ አሁንስ ከእነዚህ ሂደቶች ምን መልካም ነገር ሊወሰድና ሊኃለብት፤ ምን ክፍተቶችስ ታርመው ሊስተካከሉ ይገባል? የሚለውን ወስዶ ዛሬ ላይ የሚነሳውን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት ጥያቄ በልኩ ለመመለስ እድል ይገኝበታል።

በተመሳሳይ ሌሎች የሰላምና ፀጥታ፣ የዴሞክራሲ፣ የመልካም አስተዳደር፣ የልማት፣ የእኩል ተጠቃሚነት፣... ጥያቄዎች የዚህ ዘመን ጥያቄዎች ብቻ ያለመሆናቸውን ለመረዳት እድል ከመስጠቱ ባሻገር፤ እነዚህን ጥያቄዎች በየዘመናቱ ለመመለስ የተሄደባቸውን ርቀቶች ለመመልከት፣ ከእነዚህ ልምድ ቀምሮና ከዘመኑ ጋር አስማምቶ ለመስራት እድል የሚሰጥ ነው። ይህ ደግሞ በተለይ ከለውጥ ማግስት ያለውን ሁሉን አቀፍ ብልጽግና የማረጋገጥ ጉዞ በማሳካት ረገድ ልምድን በመቀመር ትልቅ አቅም ፈጥሮ ለመስራት የሚቻልበትን አውድ የሚፈጥር ይሆናል።

በመሆኑም እንዲህ አይነት ሁነት በተለይ ዛሬ ላይ የሚነሱ ዘርፈ ብዙ ጥያቄዎችንም ሆነ ችግሮች ምላሽና እልባት ለመስጠት መንገድ ከማመላከቱ ጎን ለጎን፤ ዛሬን አልፈን የምናልመውን ነገ ለመስራት ያሉብንን ፈተናዎች፣ ያስመዘገብናቸውን ድሎችም ሆነ ያሉንን እድሎች በወጉ እንድንለይ የሚያደርግ ነው። ምክንያቱም የትናንቱ ጉዞ ለዛሬው መሰረትም ትምህርትም እንደሚሆን ሁሉ፤ ከትናንት ተምረን ዛሬ ላይ የምናኖረው መልካም መሰረት ለነገ መዳረሻችን ጽኑ አምድ ሆኖ ያሻግረናል። ለዚህ ደግሞ ነገ ምን ለመሆን አሰበናል? ሕልማችን ጋ ለመድረስ ምን እንዴትስ መስራት አለብን? በሂደቱስ ማን ምን መስራት አለበት? የሚሉና መሰል መሰረታዊ ጥያቄዎችን በመመለስ ጉዟችን በተባበረ አቅም እንዲፋጠንና እንዲሳካ ያደርግልናል። ስለሆነም "ስለ ኢትዮጵያ" መርሃ ግብር የኢትዮጵያችንን ትናንት ተረድተን፣ ዛሬን ተባብረን ነጋችንን እንድንሰራ መንገድም አቅምም የሚያቀብል እንደመሆኑ፤ ሊዘልቅም ሊሰፋም ይገባል።


ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

# “ፖለቲከኞች ችግሮቻችሁን ይዛችሁ ወደሃይማኖት ተቋማት አትጠጉ”

**-ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደሰ**

**የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ጸሐፊ**



**እፀገነት አክሊሉ**

ኢትዮጵያን በዓለም አደባባይ ከፍ ብላ እንድትታወቅ ካደረጉ ነገሮች መካከል በውስጧ ያሉ ሀይማኖቶች ተከባብረው፣ ተዋደውና ተቻችለው በጋራ መኖራቸው ግንባር ቀደሙ ነው። ይህ የአብሮነት ማሳያ ዘመናትን ሲሻገር ቢመጣም ዛሬ ላይ ይህ አንድነት እንቅልፍ የነሳቸው አንዳንድ አካላት ይህንን አንድነት ለማደፍረስ እና የእምነቱን ተከታዮች ለማናቆር የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደር ይስተዋላል፡፡ በዚህ የተነሳም በሃገራችን አልፎ አልፎ የሚነሱ ግጭቶች ይስተዋላሉ፡፡

በሌላ በኩል በሃገራችን እነዚህ የተለያዩ ሃይማኖቶች ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት እና በጋራ ጉዳዮቻቸው ላይ በጋራ ለመስራት የሚያስችል ጥምረት ፈጥረው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ይህ የጋራ ተቋማቸውም የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ነው፡፡ እኛም በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሃገራችን ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ የሚከሰቱ ችግሮች መነሻ ምንድነው፤ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሃይማኖት ተቋማት ሚና ምንድነው፤ ይህንንስ ሚናቸውን በምን ያህል መጠን እየተወጡ ነው፤ በሚሉና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከጉባኤው ጠቅላይ ጸሃፊ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ ጋር ቆይታን አደርገናል፤ መልካም ቆይታ፡፡

**አዲስ ዘመን ፦ በኢትዮጵያ ያሉ የተለያዩ እምነቶች አብሮ በመኖር ሂደት ውስጥ ያላቸውን የቆየ ታሪካዊ ዳራ እንዴት ይገልጹታል፤**

**ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ፦** በኢትዮጵያ የሃይማኖቶች የአብሮነት ታሪክ ከሺ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ መሆኑን ሁሉም ያውቃል።በተለይም እስልምናና ክርስትና ሃይማኖቶች ከሺ አራት መቶ ዓመት በላይ ያስቆጠሩ መሆናቸው ይታወቃል።እስልምና ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ንጉስ እንዲሁም መላው ዜጋ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ቢሆኑም እንኳን የእስልምናው ዋናው መስራች ነብዩ መሐመድ ተከታዮቻቸው በአረብ አገርና በመካከለኛው ምስራቅ የተለያዩ እንግልቶችና ግፎች ሲደርሱባቸው እንዲሁም እምነቱ ከአለም ጋራ ሲያጣላቸው ወደ አበሻ ምድር ሄዳችሁ ተጠለሉ መባላቸው ይታወቃል።

በመሆኑም ኢትዮጵያ በዓለም ፊት በመቻቻል እሴት በተለይም በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት መካከል ትልቅ ቦታ ያላት አገር ነች። ከዚህ አንጻር የመቻቻል ታሪካችን ትልቅ ቦታ ይዞ አብረንም ለሺ አመታት ኖረናል፤ እየኖርንም ነው። ይህንን መሬት ከማውረድ አንጻር በተለይም ለሙስሊሞቹ ማምለኪያ ቦታ እስከመስጠት እንዲሁም የመቀበሪያ ቦታ እንዲያገኙ እስከማድረግ ፤ በአንጻሩ ለክርስቲያኑም የመቀበሪያ አጸደ የቤተክርስቲያን መግንቢያ ቦታ እስከመስጠት እና በግንባታው ላይ እስከመሳተፍ የደረሰ ቁርኝት እንደነበራቸው ይገለጻል።ይህ ደግሞ አሁን ድረስም ቢሆን አብሮን ያለ ታሪካችን ነው።

ከዚህ አንጻር የመቻቻል እሴቶቻችን ተቻችሎ ከመኖር እስከ መዋለድ ድረስ በአንድ ቤት ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተስማምተው እስከመኖር ድረስ ይደርሳል።ይህ ደግሞ የትም አለም ላይ የማናየው የእኛና የእኛ ብቻ የሆነ ነው ብለን መውሰድ እንችላለን ።ይህ ደግሞ በጣም በአለም ላይ በመቻቻል እንዲሁም በመከባበር ላይ ያላት ልምድና ተሞክሮ የሌለ መሆኑን ያሳያል።ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ ለሌሎች የአለም አገራት ጥሩ ማሳያ ናት ብለን ብንወስድ ምንም ማጋነን የለውም።እንግዲህ ይህ ነው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የመቻቻል እሴታችንን በጣም የላቀ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን የሚያሳየው።

**ኢትዮጵያውያንን ለመነጣጠል መሞከር በራሱ ለእኔ ከንቱ ድካም ነው**

በነገራችን ላይ ከላይ የጠቀስኳቸው የመቻቻል አብሮ የመኖር ሁኔታን የሚያሳዩ ገለጻዎች በጣም ከብዙ በጥቂቱ እንደሆኑም ሊታወቅ ይገባል።ምክንያቱም የእኛ መቻቻል ካለው የረጅም ዘመን ታሪክ አንጻር በአጭሩ ተገልጾ የሚያልቅ ስላልሆነ።

**አዲስ ዘመን ፦ በዓለም ላይ የግሎባላይዜሽን መስፋፋት በእምነቶች ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተፅዕኖ እንዴት ይታያል፤**

**ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ፦** ይህ ነገር ምናልብትም እንደ አረዳዱ የሚወሰን ይመስለኛል።ምናልባትም ከስልጣኔ ጋር አያይዘን የምንወስዳቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ ።በተለይም ደግሞ ከስልጣኔ ጋር ተያይዞ በፊት የነበረንን የጋራ እሴቶቻችንን የመሸርሸር፣ የማጠልሸትና ያልነበሩንን አዳዲስ ተሞክሮዎች እያስተናገድን እንደሆነ ይታያል።

ለምሳሌ አብሮ የኖረን ህዝብ አብሮ እንዳይኖር ከማድረግ አንጻር አዳዲስ እሳቤዎች አዳዲስ አስተምሮዎች ጠልቀው እየገቡ ነው። ነገር ግን እነዚህ ሁኔታዎች በእኛ በሀይማኖት ተቋማት ቦታ እንደሌላቸውና እነዚህ ባዕድ ጥገኝነቶች እንዲሁም መሰልጠን እየተባለ ወደማክረርና ጽንፍ የመውጣት ከእኔ ውጪ ሌላ አይኑር፤ ለዚህች ምድር የማስፈልጋት እኔ ብቻ ነኝ የሚሉ እሳቤዎች በሰዎች ላይ እየነገሱ መምጣታቸው ሁኔታው መጠፋፋት ካልሆነ በቀር አብሮ ለመኖር አያበቃንም።ከዚህ አንጻር እያንዳንዱ ሃይማኖት ውስጥ አስተምሮውን እየተቀላቀሉ የመጡ ነገር ግን መሰረታዊውን አስተምሮ የማይዳስሱ የማይወክሉ እሳቤዎች አሉ።ይህ ደግሞ በእኛ ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ በፍጹም ቦታ ሊኖረው የማይችል እኛ ኢትዮጵያውያንን የማይወክል የቀደመ ማንነታችንን የማይገልጽ ነው።እኛ ተዋልደናል፣ ተጋብተናል፣ ተጋምደናል፣ ተዋህደናል፤ በመሆኑም እኛን ኢትዮጵያውያንን ለመነጣጠል መሞከር በራሱ ለእኔ ከንቱ ድካም ነው።

እዚህ ላይ አንድ ምሳሌ ባነሳልሽ ሰርገኛ ጤፍ አለ፤ ይህ ጤፍ ነጩ ከጥቁሩ የተደባለቀ ነው፤ ለቅሜ አንዱን ከሌላው ልለያየው ማለትም ትርፉ ድካም ካልሆነ በቀር በፍጹም የሚታሰብ አይደለም።ኢትዮጵያውያንም እንደዛ ነን። ሁላችንም የየራሳችን የሆነ እምነት አመለካከት እንዲሁም ማንነት ያለን ህዝቦች ነን፤ ይህንን እኛነታችንን ይዘን ደግሞ አብረን ስንኖር ቆይተናል፡፡ ወደፊትም እንኖራለን። ከዚህ አንጻር ሁላችንም ስልጣኔ የሚባለው ነገር ባመጣብን ጣጣ ሳንነጠል ጥሩ ጥሩ ነገሮችን እየወሰድን የማይወክልንና ከእኛነታችን ውጪ የሆኑትን ነገሮች እያስወገድን አባት እናቶቻችችን ከኖሩት በላይ ተዋደን ተስማምተን እርስ በእርሳችን ተከባብረን መኖር ነው ያለብን።አንዳንድ አስተምሮውን ተቀላቅለው የመጡ ከመሰረታዊው ሃይማኖታዊ እሴቶች ያፈነገጡ መገዳደልን፣ መፈነቃቀልን፣ መጠላላትን፣ ከእኔ በቀር ሌላ አይኖርም ማለትን አላስፈላጊ መሆናቸውን ተገንዝበን መኖር አለብን።

**አዲስ ዘመን ፦ በሃገራችንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የእምነት ተቋማት በተለያዩ ምክንያቶች በመጤ ባህሎች የመዋጥና ከአስተምህሮ ውጭ የሆኑ ድርጊቶች የሚፈፀሙበት ሁኔታ እየሰፋ መምጣቱ ይነገራልና ይህንን እንዴት ይገልጹታል፤**

**ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ፦** እዚህ ላይ ከአስተምሮ ውጪ የግል ፍላጎቶች ሊመጡ የቻሉት ቤተ እምነቶቹ ስላልተፈተሹ ነው።በእኔ እምነት ኦርቶዶክስም ስለ አስተምሮዋ ልትፈትሽ ሃይማኖቱ ከሚፈቅደው ውጪ የሚሰጥ አስተምሮ ካለ ይህ ከእኔ ፍቃድ ውጪ ነው ብሎ መሞገት ያስፈልጋል።በሙስሊሙም በተመሳሳይ ወጣ ያሉ አብረን ተቻችለንና ተከባብረን እንዳንኖር የሚያደርጉ ትምህርቶች ካሉ መሰረታዊ ፍላጎታቸው ይህ አለመሆኑን ማስረዳት፣ተው ማለት መከልከልና ማገድ ይገባል።እዚህ ላይ ሁላችንም እንደየእምነታችን አብረን እየኖርን ነገ ሰማያዊ መንግሥትን መውረስ ከሆነ ፍላጎታችን ሳንገፋፋ ሳንጣላ በጣም በጥንቃቄ ባዕድና ከመሰረታዊው አስተምሮ ያፈነገጡትን በመመከት ቤተ እምነቶች ሚና ሊኖራቸው ይገባል ብለን እየሰራን እንገኛለን።በመሆኑም ሁሉም ቤተ እምነት ይህንን ባዕድ የተቀላቀለ ኢትዮጵያዊነትን የማይገልጽ የእኛ እሴት ያልሆነና አብሮነታችንን የማያሳይ ሁኔታን መሰረታዊውን አስተምሮ በማንሳት መሞገት፣ መውቀስና እኛን አይወክልም ማለት ይጠበቅብናል።

**አዲስ ዘመን ፦በሃገራችን በቀደመው ዘመን የሃይማኖት አባቶችና ታላላቅ የሃገር ሽማግሌዎች የመደመጥ አቅም ከፍተኛ እንደነበር እና ይህ ግን አሁን አሁን እየቀነሰ መምጣቱ ይነገራል፤ ስመሆኑ ይህ ምን ያህል እውነትነት አለው፤ እውነት ከሆነስ ምክንያቱ ምንድነው፤**

**ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ፦** ይህ እንግዲህ በተለይም ስልጣኔ ብለን ቅድም ካነሳነው አንጻር ሊታይ የሚችል ነገር ነው።አሁን አሁን እየመጡ ካሉት የቴክኖሎጂ ውጤቶች ማለትም ማህበራዊ ሚዲያዎች

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

ጋር አቀራኝቶ ማየትም ሳያስፈልግ አይቀርም። እዚህ ላይ ትልልቆቹ አባቶቻችንና ጸሃፊያን እነዚህን ማህበራዊ ሚዲያዎች አይጠቀሙም ፤እነሱን የምናገኝበት መንገድም የለንም። አሁን የሚያወሩ፣ የሚናገሩ፣ የሚንጫጩ ሁሉ በዚህ ማህበራዊ ሚዲያ ውስጥ ያሉ አካላት ናቸው። እየገነኑ የመጡትም ብዙ ተከታይ ያፈሩትም ህዝቡ ቁጭ ብሎ በሚውልበት መንገድ በመምጣታቸው ነው።እነዚህ ሰዎች በልመና በተለያዩ መንገዶች ተከታይ ያሰባስቡና ቆየት ብለው ለጥፋት ይጠቀሙበታል። እንዳጀማመራቸው ሰላማዊ ይመስላል፤ ነገር ግን ያገኙትን ተከታይ የሚጠቀሙበት አፍራሽ ለሆነው አስተሳሰባቸው ማራመጃነት ነው። ሁኔታቸውም ተሰሚነት ስለሚሰጣቸው ትንሹን ትልቅ እያደረጉ በማቅረብ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ይሰበስቡበታል።

ለምሳሌ አሁን ሀጂ ሙፍቲ ምንም ዓይነት የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ አይደሉም፤ በመሆኑም በመገናኛ ብዙሃን በኩል ካልሆነ እንደዚህ ነው ብለው የሚያስረዱበት መንገድ ጠባብ ነው።ሌሎቹም የሃይማኖት አባቶች እንዲዚሁ ናቸው፡፡ በመሆኑም አሁን በአገራችን ለምንመለከተው ጽንፍ የወጣ ችግር መባባስ ምክንያት እየሆኑ ካሉ ነገሮች አንዱ የማህበራዊ ሚዲያው ነው። ከተቋም ይልቅ ግለሰቦች እየገነኑ መምጣታቸው ነው። እነዚህ ግለሰቦች ደግሞ ራሳቸው ተቋም አድርገው ራሳቸውን ተራራ ላይ ያስቀምጣሉ፤ እነሱን የሚከተሉ ደግሞ እነሱው በመሯቸው መንገድ ይፈሳሉ ማለት ነው።እነዚህ ሰዎች እኮ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን የሚያሳዩ ቢሆኑ፤ ተዋደዱ፣ ተቃቀፉ፣ የሰላም እሴቶችን ገንቡ፣ ተካፍለህ ብላ፣... የሚሉ ቢሆኑ እኮ ምንም አልነበረም፤ ነገር ግን አብዛኛውን የሚመሯቸው ወደ እሳት ነው።ሂድ አቃጥል፣ መንገድ ዝጋ፣ ግደል፣ አፈናቅል፣ ወዘተ ነው። በመሆኑም አሁን ላይ መደረግ ያለበት እንዲሁም እነሱን የሚከተለውም ሆነ ሌላው ሰው ማድረግ ያለበት ጥሩውን ከመጥፎ እሳቱን ከውሃ መለየት ነው።

አባቶች አሁንም በጾም ጸሎታቸው በአስተምሯቸው በትህትናቸው በጠቅላላው በበጎ ስራቸው ላይ አሉ። የቀነሰ ነገርም የለም።ከወንበራቸውም አላፈነገጡም። የምናያቸው ነገሮች ግን አለም ሌላ መንገድ እየተከተለች ስለሆነ ዛሬ አሜሪካን ላይ የሚደረገው ነገር በኢትዮጵያ ገጠር ውስጥ ይታያል ።በመሆኑም እሱ የፈጠረው ተጽዕኖ እንጂ እኛ እንደሚመስለን አባቶች እየተሰሙ ስላልሆነ እነሱም እየመከሩ ስላልሆነ አይደለም።

በሁሉም ሃይማኖት ውስጥ ያሉ ትልልቅ አባቶች ማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ አይደሉም።ይህ ሁኔታ የፈጠረውን ክፍተት ደግሞ ለእምነቱ ቀናይ በመሆኑ በበጎ እሳቤ ልባቸው በተሞላ ምእመናን የሚካካስ ይሆናል።ነገር ግን አሁንም አባቶች ለአገራችን ሰላም ለህዝባችን አንድነት፣ አብሮነት፣ መቻቻል፣ ለሃይማኖቶቻችን ተከባብሮና ተዋዶ መኖር እየሰሩ፣ እየጸለዩ፣ እየመከሩ፣ እየዘከሩ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

**አዲስ ዘመን ፦ በሌላ በኩል በሃገራችን የሃይማኖቶች መቻቻል ለዓለም ጭምር ተምሳሌት የሚሆን እንደነበር በተለያዩ አጋጣዎች ይገለፃል፤ አሁን አሁን ግን በሃይማኖት ስም ግጭቶች ጭምር ሲከሰቱ ይሰማል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሃይማኖትን ለፖለቲካ መጠቀሚያነት የማዋል ሁኔታ መኖሩን የተለያዩ ሰላም ወዳድ ዜጎች ጭምር ይገልጻሉና ይህንን እንደ ሃይማኖት ተቋማት ህብረት እንዴት ይመለከቱታል?**

**ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ፦** ፖለቲካና ሃይማኖት ለመጋባት ከድሮም ጀምሮ ቢሆን ጥረት ያደርጋሉ፤ ሲጋቡም አላስፈላጊ ነው ብዬ አስባለሁ።ምክንያቱም ብዙ አብረው መጓዝ አይችሉም ፤መንፈሳዊ ተቋማት የሚሰብኩት ሰማያዊ መንግሥትን ነው፤ ፖለቲከኞች ደግሞ ለማኖር የሚሰብኩት ምድራዊ ንጉስን፣ ስልጣንና ስርዓትን ነው።በመሆኑም ሁለቱም እንደሚከተሉት አካሄድ ሁሉ ልዩነታቸውም የሰማይና የምድር ያህል ነው።በመሆኑም እነዚህን ማጋባት በጣም ከባድ ነው። ነገር ግን ሰማያዊውም ምድራዊውም ተባብሮ መስራት



ይችላሉ ።ለሰላም ስለሰላም አብሮ መዘመር ይችላሉ ።ስለልማት አብሮ መስራት ይችላሉ።ነገር ግን ከዛ ባፈነገጠ መልኩ አብረው ሆነው ሚናቸውን ተቀያይረው ቢታዩ ምንም ጥቅም ካለመኖሩም በላይ የሚሰማቸውም አይኖርም።

በመሆኑም ሁለቱም ሳይቀላቀሉ መቀጠል አለባቸው እላለሁ። አሁን ላይ ግን ሁለት ካባ መልበሳቸው ነው አስቸጋሪ እየሆነ የመጣው። በቤተ መንግስት ውስጥ ሆነው መንፈሳዊ ካባ ይለብሱና ነገሮችን ሁሉ ስብከት ያደርጉታል፤ በኋላም አድማጭ ያጣሉ።በቤተ እምነት ውስጥም ሆነው የፖለቲካ ስብከት የሚሰብኩ ነገር ግን መንፈሳዊ ካባ ያጠለቁ ሰዎች ተቀላቅሎባቸው ብዥታ ውስጥ ስለገቡ ነው። በመሆኑም እነዚህ አካላት ሚናቸውን መለየት አቀማመጣቸውን አሰላለፋቸውን መለየት ይገባቸዋል።ምክንያቱም እነሱ ባቀላቀሉት ልክ የሚሄድ ከሆነ ተከታዮቻቸውም ብዥታ ውስጥ ይወድቁባቸዋል።ይህንን ማጥራት በጣም አስፈላጊ ነው።

ግጭቶች ሲፈጠሩ ወደሃይማኖት ሊያላክኩ የሚፈልጉ ፖለቲከኞች ዋና አላማቸው የሰውን ስስ ስሜት መቀስቀስው ነው ።ይህንን የሚያደርጉት ደግሞ ሰዎች ለሃይማኖታቸው ስስ በመሆናቸው ሃይማኖትህ ተነካ ስለ ሃይማኖትህ ብትሞት ትጸድቃለህ ሲባል ቶሎ ይነሳል፤ አያገናዝብም፣ ምክንያታዊም አይሆንም፣ በመሆኑም ሰውን ወደስሜት ለማስገባት ሃይማኖትን ሽፋን ያደርጉታል።በማንነቱም ሲመጡበት ስሜቱ ተመሳሳይ ነው፤ በመሆኑም እነዚህን ሁለቱን መቀላቀል በጣም ከባድ አደጋም እንዳለው ፖለቲከኞች ያውቃሉ።ፖለቲከኞች ደግሞ ሁኔታዎችን አስልተው አጥንተው ነው የሚንቀሳቀሱት፡፡ ምንም የማያውቀው ህዝብ ደግሞ ይቀላቀልበትና ዝም ብሎ ይከተላል፡፡ መጨረሻ ላይ ግን እሳቱ ከነደደ በኋላ ገደል ላይ መሆኑ ሲገባው ነው ወደኋላ የሚመለሰው።ይህ ደግሞ ንብረት ከወደመ የሰው ህይወት ከጠፋ በኋላ ይሆናል።ስለዚህ ፖለቲከኞች ችግሮቻችሁን ይዛችሁ ወደሃይማኖት ተቋማት አትጠጉ፣ አትቀላቀሉ። አሁንም ምክራችን ይኸው ነው።

**አዲስ ዘመን ፦ በሃገራችን ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት የሃይማኖት አባቶች እና የእምነት ተቋማት መሪዎች ሚና ምን መሆን አለበት፤ ይህንን ሚናቸውንስ ለመወጣት ምን ማድረግ አለባቸው ይላሉ?**

**ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ፦** የሃይማኖት አባቶች ሚናቸው የታወቀ ነው፤ ተልዕኳቸውም ሰማያዊ ነው። የሚያወርሱትም የሚወርሱትም ሰማያዊ ነገር ነው። ፖለቲካ ምድራዊ ነው። ሰማያዊ ሆኖ አያውቅም። በመሆኑም ሁሉም ሚናቸውን በትክክል ሊያውቁ ይገባል።

**በቤተ መንግሥት ውስጥ ሆነው መንፈሳዊ ካባ ይለብሱና ነገሮችን ሁሉ ስብከት ያደርጉታል፤ በኋላም አድማጭ ያጣሉ።በቤተ እምነት ውስጥም ሆነው የፖለቲካ ስብከት የሚሰብኩ ነገር ግን መንፈሳዊ ካባ ያጠለቁ ሰዎች ተቀላቅሎባቸው ብዥታ ውስጥ ስለገቡ ነው**

ከዚህ ውጪ ግን የእምነት ተቋማት ከመለኮት የተሰጠን ተልዕኮ አለ ።የተሰጠንን ተልዕኮ ወደመሬት አውርደን ተግባራዊ ስራን ምእመናኖቻችን ላይ መስራት ይጠበቅብናል። ለምሳሌ በክርስትና እምነት ምዕመናን በስጋቸው እንዲጠበቁ፣ በመንፈሳቸው እንዲታደሱ፣ ለሰማያዊው መንግሥት እንዲበቁ ማድረግ ተልዕኳቸው ነው። በመሆኑም ካህኑ፣ ዲያቆኑም፣ ሰባኪውም ፣ ጳጳሱም ማድረግ ያለበት ይህንን ነው ።

በተመሳሳይም የእስልምና እምነት ተከታይ ወንድም እህቶቻችንን ለአላህ መንግሥት እንዲበቁ ለማድረግ ከክፉ ስራ ተቆጥበው ለወገናቸው አዝነው ተዛዝነው እንዲኖሩ በጾም ጸሎት እራሳቸውን ጠብቀው ህሊናቸውን ለፈጣሪያቸው እንዲያስገዙ ለማድረግ የኡለማው የሼሁ የኡስታዙ ስራ ነው ብዬ አስባለሁ። ከዚህ ውጪ ሌላ ተልዕኮ አለ ብዬም አላስብም።ፉክክር ውስጥ መግባት አለብንም ብዬ አላስብም።

በመሆኑም ወደ ትብብር መጥተን እንደ ድሮ አባቶቻችን ተከባብረን ሃይማኖታዊ አስተምሮው በሚያዘው መሰረት መኖር አለብን የሚል ሃሳብ ነው ያለኝ። እንደ ሃይማኖት አባትም በዚህ ልክ ከሄድን ምንም ዓይነት ግጭት በአገራችን ላይ አናይም እላለሁ።

**አዲስ ዘመን ፦ በአሁኑ ጊዜ አንድ ሰው ተነስቶ የኔ እምነት እንዲህ አይነት ችግር ደረሰበት ሲል ተከታዩ ቆም ብሎ ከማጣራት ይልቅ ለግጭት የሚነሳሱ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም፤ ይህ ደግሞ ከፍ ያለ አደጋ አለውና እንደው ከግጭት በፊት ሰዎች ማድረግ ስላለባቸው እና ስለስክነት በጥቂቱ ቢነግሩን፦**

**ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ፦** አዎ ሰው ሰውነቱ የሚታወቀው ወይንም ደግሞ ከእንስሳት የሚለየው አርቆ በማሰቡ ይህንን ባደርግ ነገ ምን ሊፈጠር ይችላል፤ ባላደርግስ በእኔና በአገሬ ላይ ምን ጥቅም አመጣለሁ የሚለውን ቆም ብሎ ማሰብ በመቻሉ ነው።አልያ ግን ስሜት የሚነዳው የፈለገውን ነገር በሚፈልገው ሰዓት ካላገኘ የሚያመው ሌሎችን አስተባብሮ አገርን ለማፍረስ ወገኑን ለመጉዳት ጦር የሚሰብቅ ድንጋይ የሚወረውር ቅዱስ የሆኑ የሃይማኖት ተቋማት ላይ እጁን የሚያነሳና በእሳት የሚያቃጥል ሰው እውነት ለመናገር እንኳን ከሰው ከእንስሳቱም ያነሰ ነው የሚሆነው።

በመሆኑም ማንም ሰው ነኝ የሚል፤ በተለይም ደግሞ ለእምነቴ ለሃይማኖቴ ቀናይ ነኝ የሚል አካል እርጋታ ሊኖረው የግድ ነው።ምክንያቱም መንፈሳዊነት በራሱ እርጋታን የሚጠይቅ ነገር በመሆኑ።ቤተ እምነቶቻችን ጋር ስታይ እርጋታ ያለ ነገር ነው የሚስተዋለው እንደ መርካቶ ውክቢያ የለም፤ አሁን በያዝነው ልክ ግን ቤተ እምነቶቻችንን መርካቶ ካደረግናቸው በጣም ከባድ ነው። ነገሮችን ማጤን ስክነት በጣም ወሳኝ ነው።“ስድስት ጊዜ ለካ በሰባተኛው ቁረጥ” ነው የሚለው መጽሃፉም፤ ይህ አባባል ቀላል አይደለም፤ በጣም እንድንሰክን እንድንረጋጋ የሚያመለክት ነው። ፈጣሪ እኮ ሲፈጥረን አንድ አፍ ሁለት ጆሮ ነው የሰጠን፡፡ ምናልባት እኮ አንድ ጆሮም በቂያችን ነበር፡፡ ነገር ግን ከመናገራችን በፊት ማድመጥ በደንብ ማሰብ ያዳመጥነውን ደግሞ በእርጋታ በአንድ አፋችን ማውራት እንዳለብን ሲያሳየን ነው።

በመሆኑም መረጋጋት ፣ማሰብ፣ መስከን ከሁሉም ይጠበቃል። አንዳንድ ጊዜ የሚመጡ ንፋሶችንም ጥግ ይዞ አልያም ጎንበስ ብሎ ማሳለፍ ሊያስፈልግ ይችላል። ምክንያቱም የሚመጣው ንፋስ አንዳንድ ጊዜ አዋራ ድንጋይ ሊቀላቅል፣ ዝናብም በረዶም ሊኖረው ይችላል። በመሆኑም ይህንን ሁኔታ በጥንቃቄ ማሳለፍ ካልተቻለ ለአደጋም መጋለጥ ይኖራልና በደንብ መጠንቀቅ በጣም መዘጋጀት አስፈላጊ ነው።

አንድን ውሳኔ ከመወሰን በፊት ደጋግሞ ማሰብ ውጤቱን መገመት በጣም ያስፈልጋል፤ ካለፈ በኋላ የሰው ህይወት ከጠፋ ንብረት ከወደመ ቤተ እምነት ከተቃጠለ በኋላ ጸጸት ነው ትርፉ፤ ምን ሆኜ በምን ቀን ነው ያደረኩት የሚባልበት ጊዜ ይመጣል። ለሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ስራ ከመስራት መቆጠብ ከሁላችን ይጠበቃል።

**አዲስ ዘመን ፦ ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ፦** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ከታሪክ ኩራትና ሙግት ፋታ እንውሰድ

**ታሪክ ማለት...**

ሃገር እንደ ሃገር የቆመው በትናንቱ መደላድል ላይ ስለመሆኑ ገላጭ አያስፈልገውም። የዛሬ መሠረቱ ትናንት ስለመሆኑም ደጋግመን ጽፈናል። ትናንትን ትናንት ያሰኘውም ጠቅልሎ የያዘው ታሪኩ ነው። ዛሬንም ዛሬ ያሰኘው ኑሯችን ሲሆን፤ ነገን ነገ የሚያሰኘው ደግሞ በተስፋ መታጨቁ ነው። ስለዚህም ትናንት ስብዕናችንን ቀርጾ ለዛሬ አቀብሎናል። ዛሬ ከኑሮ ጋር እያታገለ ያፋልመናል። ነገ በተስፋ እንቁልልጮሽ እያማለለ እንድንናፍቀው ያባብለናል፤ ሲለውም እያስበረገገ ያባንነናል። እነዚህ ሦስቱ የጊዜ ገጾችና ምዕራፎች ሊገለጡና ሊመረመሩ የሚገባቸው እንደየባህርያቸው ነው የሚባለውም ስለዚሁ ነው።

"በእኔና በስብሐ የማይበረታ የለም" አለ ይባላል፤ በወገኖቹ መገፋት የተማረረ "እከሌ" የማይባል የሃይማኖት አገልጋይ። "ስብሐ"፡- ስብሐት ለአምላክ፣ ምሥጋና ለፈጣሪ እንደማለት ነው። ይህንን ቃል አብዛኛው የክርስትና እምነት ተከታይ በሰርክ ጸሎቱና ማዕዱን ከመቁረሱ አስቀድሞ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት የአፍ ማሟሻው ነው። የተማረም ይሁን ማይም ምዕመን ይሄንን ቃል ሳይጠራ ውሎ አያድርም። ከቤተ እምነት ደጀሰላም እስከ እያንዳንዱ ግለሰብ ደጃፍ ፈጣሪ የሚመሰገንበትን ይህንን የሁሉም የሆነ አባባል ለማስታወስ የተፈለገው አንድ "ብጤ ጉዳይ" ለማስታወስ ተፈልጎ ነው።

ነገረ ታሪክም እንዲሁ ልክ እንደ "ስብሐ" የፈለገ ሁሉ ሲያነሳውና ሲጥለው የሚውል የጋራ ጉዳይ ከሆነ ሰነባብቷል። ማንም ተነስቶ ታሪክ ልተርክ ቢል "የት ታውቅና"፣ ወይንም "መቼ ደረስክበትና" አለበለዚያም "ማስረጃህን አቅርብ" ተብሎ አይገሰጽም፣ አይወቀስምም። ማንም እየተነሳ የታሪክን እውነታ ቢሰብር፣ ቢያጣምምና እንዳሻው ጭራና ቀንድ እየጨመረ ከራሱና የራሱ የክፋት ዓላማ ማስፈጸሚያ ሰሌዳ ላይ ቢጽፍና ቢስል ወይንም ቢያሾፍና ቢያላግጥ የአርምሞ ትዝብት ይተርፈው ካልሆነ በስተቀር ተቆጭም ሆነ ተሟጋች እስከማይኖር ድረስ "የታሪክ ጉዳይ እንደረከሰ የገበያ ሸቀጥ" የሚያፍሰውና የሚበረታበት ሁሉም ዜጋ ከሆነ ሰነባብቷል። በተለይም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ።

"ታሪክ አይጣመም! ታሪክ አይወላገድ! ወዘተ." እያለ በመጮኽ የሚገስጽ አልጠፋም ቢሰኝ እንኳን ለወቀሳውና ለአራሚነት ፈጥነው ምላሽ የሚሰጡት "እኛ የተሻለ እናውቃለን" የሚሉ ሰዎች እንጂ "እስቲ እነ እከሌ ይጠየቁ" ተብሎ ሁነኛ ምስክር ለመቁጠር እንኳን እያዳገተ ስለመሆኑ ዋቢያችን የውሎ አምሽቷችን ገጠመኝ ነው። ስለዚህም የስብሐን ምሳሌ በመዋስ በትናንቱ ታሪክ ላይ መሟገቱ ዋና ጉዳይ ሆኖ ዛሬ መዘንጋቱ ሆድ አብሶ ግድ ያለን ዜጎች "በእኛና በታሪክ የማይበረታ የለም" ብለን አባባሉን ከዐውዳችን ጋር ብናስማማ "ይደልዎ!" ቢያሰኝ እንጂ የሚያስወቅስ አይመስለንም። በተለይም በዚህ ግራ ቀኙ በጠፋን ወቅት፣ ከዕለት ኑሮ ጋር መፋለሙና በኃዘን መርዶና ጨርቅ መቆራመዱ ያነሰን ይመስል በነበር ታሪክ ላይ ዱላ እያሳረፉ የሚያጯጯኹትን ሃይ የሚልልን ኃይል አጥተን እንዲሁ እንደተብሰለሰልን "ኑሮ ካሉት..." እያልን፤ ኑሮን እንገፋለን።

በአጥናፈ ዓለማችን ዙሪያ-ገብ ላይ የተመራመሩ፣ የተራቀቁና ለሰዎች ልጆች በጎ በመዋላቸው ከሚጠቀሱት ብርቅዬ የምድራችን የዕውቀትና የጥበብ ፈርጦች መካከል "ታሪክ ማለት..." እያሉ ድንጋጌና ፍቺ ያልሰጡት ይመረጡ

**ቢመርም፣ ቢኮመጥጥም አፍረታችንን ሳንሸሽግና ያደግንበት የማለባበስ ባህል ሳይጫነን በታሪክና በባህል የተጀቦንባቸውን ገመናዎቻችንን ልንገላልጥና ልንወያይባቸው ይገባል። የተኮፈስንባቸውንና በሰንኮፎቻቸው የተለከፍንባቸውን ማኅበራዊ ደዌዎችንም እያፈረጥን ለመፈዋወስ መጨከን ይኖርብናል። የሚበጀው ከታሪክ ኩራታችንንና ሙግታችን ለጊዜው ፋታ በመውሰድ ወደ ኅሊናችን ተመልሰን ለፈውስ መሥራቱ ላይ ነው**

ቢባል ልንቆጥር የምንችለው ጥቂቶችን ብቻ ነው። ለምን ቢሉ የታሪክ ባለሙያዎች ብቻም ሳይሆኑ የበርካታ የሙያ ዘርፍ ባለቤቶች ሳይቀሩ ስለ ታሪክ ብያኔ ቁጥር ስፍር የሌለው ድንጋጌ ለመስጠት ሞክረዋልና። ዛሬም ድረስ እየሰጡ እንደሚገኙ ቴክኖሎጂ ደጉን በማማከር ብቻ ምላሹን በቀላሉ ማግኘት ይቻላል።

ስለ ታሪክ ምንነት ከሚያወሱት ተደጋጋሚ፣ ተጠቃሽና ተወዳጅ ጥቅሶች መካከል ጥቂቶቹን ብቻ ቆንጥረን በማስታወስ ወደ መነሻ ጉዳያችን እናቀናለን። "ታሪክ በአንቱታና በግድፈቶች የተሞላ የኩነቶች ድምር ውጤት ነው።" የሚለውን አስቀድመን ሌሎቹን እናስከትላለን። "ታሪክ ያለፈ ክስተት ብቻ ሳይሆን ከአንድ አቅጣጫ የተቃኘ የኃላፊ ጊዜያት ጠቋሚ ካርታ ጭምር ነው። አንተ ዘመንኛው ተጓዥ ሆይ! በካርታው ካልተመራሁበት ብለህ ግብ ግብ አትፍጠር።

ታሪክ እንደ ኮምፓስ የቀደመውን መንገድ በትዝታና በነበርነቱ እንድታስታውስ፣ እንድታከብርና መሰል ስህተት በዛሬዋ ጀንበር እንዳትፈጽም የሚረዳህ ነው። ከበጎነቱም እንድትማር ያግዝሃል እንጂ እንደ አሠርቱ ትእዛዛት ከዘፍጥረት እስከ ዘመነ ፍጻሜ እንድትመራበት "በሙሴ በጽላት" መልክ ተቀርጾ የተሰጠህ መመሪያ አይደለም።" ሦስተኛ ሠልሰን እናብቃ። "ታሪክ ተገቢውን ምላሽ ሊሰጥ የሚችለው ምንና እንዴት መጠየቅ ለሚችሉት ብቻ ነው።"

**ታሪካችን እፎይ ይበል ስንል...**

ቀደምት ታሪኮቻችንን እረፍት በመንሳት በነጋ በጠባ እየጠቀስን የምንኮራባቸውንና የምንራኮትባቸውን አንዳንድ ጉዳዮች እየጠቃቀስን እንደተለመደው ጥቂት ደቂቆች መድበን ለማሰላሰል እንሞክር። "ብዙ ዜጎች በኃላፊ ታሪክ ላይ ዱላ እየመዘዙ ለመቀጥቀጥ እጅግ ብርቱ ናቸው።" ጥቂት ማከያ ሃሳብ እንፈነጣጥቃለን።

እንኳን እስትንፋሳቸው ቀርቶ አጽማቸውንም ቢሆን በአግባቡ ማግኘት ከሚያዳግት "ተወቃሽ ናቸው ከሚላቸው" ባለ ታሪኮች ጋር ፍልሚያ ካልገጠምን እያሉ የሚያቅራሩ አንዳንድ ሳይሞቅ ፈላ የነገር "ጎታዎች" ወላንሶ መግጠማቸው የጀግንነት ወኔ ግድ ስለሚላቸው ሳይሆን ፈሪ ስለሆኑ ነው። ራሱን ለመከላከል አቅም የሌለውን ታሪክና ከመቃብር በታች የዋሉ ባለታሪኮችን በሚመዙት የእብሪት ዱላ አናት አናታቸውን የሚሏቸው "የጅል ፈሊጥ" ተጠናውቷቸውና የቂም በቀል ጥማታቸውን ያረኩ እየመሰላቸው ስለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎችን በመጠቃቀስ መወያየት ይቻላል።

እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ባለፈ ታሪክ ለመጣላትና ሰይፍ ካልተማዘዝን ብለው የሚያቅራሩት ፍልሚያው አሸናፊም ይሁን ተሸናፊ እንደማይኖረው ጠፍቷቸው አይደለም። እንደ "መስቀል ጦርነትም" ከዘመን ዘመን የሚሻገር "ጠብ ያለሽ በዳቦ" ይሉት ዓይነት ኩነኔ መሆኑም ስላልገባቸው አይደለም። ይልቁንስ ይህንን በማድረጋቸው ስብዕናቸውን ለማግዘፍና ባዶነታቸውን የጋረዱ እየመሰላቸው ነው። ባይሆን ኖሮማ "ስህተት ነበር" የሚሰኘው የታሪክ ክስተት እንኳን ሊታረም የሚችለው በሰላማዊ ውይይትና ምክክር እንጂ "በቆፈሩት ምሽግ ውስጥ" ተገን ይዘው በመታኮስ መሆን አልነበረበትም። "የተሳሳተ" የሚሰኝ ታሪክን ለማረም ከሰይፍና ከጎመድ ይልቅ የሚያዋጣው ውይይት! ወይይት! ወይይት! ብቻ ነው።

የሆነው ሆኖስ እስቲ አከራካሪ ታሪኮችን ብቻም ሳይሆን ደፈርና ጠንከር ብለን "ታሪካችን" እያልን የምንኩራራባቸውንና የምንዘናጋባቸውን አንዳንድ ክስተቶች እየጠቃቀስን እንወያይ። ቀደም ባሉት ጽሑፎቼ በተደጋጋሚ ለማስታወስ እንደሞከርኩት አገራችን የታሪክ ባለጸጋ ብቻ ሳትሆን የተግባር ድሃ መሆኗንም ጭምር በአግባቡ ልንነግራት ይገባል።

ኢትዮጵያ ሦስቱን ታላላቅ ሃይማኖቶች (የአይሁድ እምነትን፣ ክርስትናንና እስልምናን) የተቀበለችው በሰላም እጆቿን ዘርግታ በፍቅር እያቀፈች እንደነበር በቀዳሚው ጽሑፎቼ ዝርዝሩን አስነብቤያለሁ። ሃይማኖቶቹ ቤትኛ ከሆኑ በኋላ ግን በረጂሙ የታሪካችን ጉዞ ውስጥ የኖሩትና የተስፋፉት ያለ እንከን ነበር ማለት ግን አይደለም። በሰላምና በፍቅር የተስተናገዱት እነዚህ የሺህ ዓመታት ባለታሪክ ሃይማኖቶች ዛሬ ዛሬ ምን ያህሉ "ከማራኪ መዓዛቸው" ጋር አሉ? ምእመናኖቻቸውስ ምን ያህል በተሰበከላቸው የፍቅርና የሰላም መልዕክት ታንጸው እምነታቸውን ለመተግበር እየጣሩ ነው? የየእምነቱ ቀኖናዎችና ትምህርቶች አማኒያኑን ወደ ፈጣሪ ለማቅረብ ምን ያህል ብርታትና አቅም አላቸው? የየእምነቶቹ "አበ ነፍሳትስ" ምን ያህሉ የሰላም ሐዋርያትና የበጎነት ተምሳሌቶች ናቸው?

በየደጀሰላሙ ምስባኮች ላይ የሚጎርፈው የየእምነቱ ትምህርትና እግዚአታስ ምን ያህሉ ወደ ፈጣሪ መንበር ደርሶ ምህረትና ፈውስ ይዞ የመምጣት መንፈሳዊ ብርታት አለው? በሃይማኖት ስም ከሚጠፋፉት ነፍሳት መካከል "የሚጸድቀው" የትኛው ነው? ንጹሑና ደሙ የፈሰሰው "አቤል" ወይንስ በሃይማኖት ቀናኢነት ደም የሚያፈሰው "ቃየል?" የበጎነቱ ሥራ በፈጣሪ መዝገብ ላይ የሚመዘገብለትስ የሌላውን ሃይማኖት ማምለኪያ ሕንጻ እያቃጠለ የፈጣሪን ስም የሚያሞግሰው ነው? ወይንስ ቤተ እምነቱ ስለተቃጠለበት እምባውን እያፈሰሰ ፍርድን የሚማጸነው?

ለእነዚህን መሰል ሺህ ምንተ ሺህ ጥያቄዎች ጥርት ያለ ምላሽ እስካላገኘን ድረስ "ከኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ዘጠና ዘጠኝ ከመቶው በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የሃይማኖት ተከታይ ነው" እያልን የምንፎክርበትን እስታትስቲክ ለጊዜው ከፊታችን ዞር አድርገን ብናስቀምጠውና ባንጠቅሰው የተሻለ ይሆናል። ለምን ቢሉ የቁጥሩ ትምክህት አዋረደን እንጂ አላከበረንም፤ አሳቀቀን እንጂ አላሳቀንም።

ስለዚህ የሃይማኖቶቻችንን ጥንታዊ አገባብና የምዕመኑን የዛሬ ቁጥር ችላ ብለን፣ ከታሪክ ሙግቱና አታካራም ፋታ በመውሰድ ራሳችንን ገለል በማድረግ ከፈጣሪያችን ጋር ብቻ በጓዳችን ውስጥ ጣጣችንን መጨረሱ ብልህነት ነው። የየሃይማኖቱ ቤተእምነቶችም ቢሆኑ "የምዕመናኖቻችን ቁጥር በሚሊዮን የሚሰላ ነው" እያሉ መፎከሩንና ማስፎከሩን ለጊዜው ተወት አድርገው እንደ ሃይማኖታዊ ባህላቸው በንስሐና በሱባዔ ከፈጣሪ ጋር ቢስማሙና ቢታረቁ ይበጃል።

ሌላውና ደማቁ አገራዊ ቀረርቷችን ከእንግዳ ተቀባይነታችን ጋር የሚያያዘው ትምክህት ነው። እርግጥ ነው በቀደምት ታሪኮቻችን ውስጥ የሚጠቀሱ አንዳንድ በጎ ተግባራት መኖራቸው ላይካድ ይችል ይሆናል። ለምሳሌ፡- የሃይማኖቶችን ወደ አገራችን መግባትና አቀባበላቸውን በተመለከተ ከላይ የጠቀስነውን ታሪክ ደግሞ ማስታወሱ አግባብ ይሆናል። በአንዳንድ የሃገራችን የገጠር አካባቢዎች የእንግዳ ክብርና በፍቅር የታጀበ አቀባበል ሙሉ ለሙሉ ተሟጦ ጠፍቷል ብሎ አፍ ሞልቶ ለመናገርም ያዳግታል። ምክንያቱም ቅሪቱ ዛሬም ድረስ ስላልደበዘዘ።

ነገር ግን እውነቱን አፍርጠን እንተማመን ከተባለ በዛሬው የአገራችን ዐውድ አንኳንስ እንግዳና የአካባቢው ነዋሪ ዜጎችስ በአንቱታ ይከበራሉ። "መጤ ስለሆንክ ከአካባቢዬ ውጣ!" እየተባሉ ስንቶቹ ለዓመታት ከኖሩበት መኖሪያቸው እየተፈናቀሉ አይደለም? ንብረታቸውስ አልወደመም? በግፍና በጥላቻስ የሺህዎች ደም ደመ ከልብ ሆኖ ቀባሪ እንኳን አጥተው የአውሬ ሲሳይ አልሆኑም? ለአንድ አካባቢ ባዕድ የሆነ ዜጋስ እንደልቡ ለሥራም ይሁን ለግል ጉዳይ ከአገሩ ጫፍ እስከ ጫፍ በነፃነት መንቀሳቀስ ይችላል? ሠርቶ ንብረት ማፍራትስ መብቱ ነው?

የዓለም ሃገራትና ሕዝቦች ዛሬ ኢትዮጵያን የሚያውቋት በእንግዳ ተቀባይነቷ ነው ወይንስ ዜጎቿን ለስደት በማበረታታትና ባዕዳን ሕዝቦች ልጆቿን "እንዲያዝሉላት" ሸክም አድርጋ በመወርወር? ቢመርም፣ ቢኮመጥጥም አፍረታችንን ሳንሸሽግና ያደግንበት የማለባበስ ባህል ሳይጫነን በታሪክና በባህል የተጀቦንባቸውን ገመናዎቻችንን ልንገላልጥና ልንወያይባቸው ይገባል። የተኮፈስንባቸውንና በሰንኮፎቻቸው የተለከፍንባቸውን ማኅበራዊ ደዌዎችንም እያፈረጥን ለመፈዋወስ መጨከን ይኖርብናል። የሚበጀው ከታሪክ ኩራታችንንና ሙግታችን ለጊዜው ፋታ በመውሰድ ወደ ኅሊናችን ተመልሰን ለፈውስ መሥራቱ ላይ ነው። ለጥሞና ጊዜ በመውሰዳችንም ስናንቆለጳጵሳቸው የኖርነው ታሪኮቻችን የትም አይሄዱብንም። የምንፎክርባቸው ባህሎቻችንም አይሸሹንም። ይኼው ነው። ሰላም ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

## በመኖ ዋጋ ንረት የሚናጠው የወተት ገበያ

**ፍሬሕይወት አወቀ**



ወተት በውስጡ በያዛቸው በርካታ ንጥረ ነገሮች አማካይነት ለሰው ልጆች ሁሉ በተለይም ለሕፃናት እጅጉን አስፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ የወተት ልማት ዘርፉ በየጊዜው እየጨመረ ከመጣው የሕዝብ ቁጥር ጋር የተጣጣመ አይደለም። በመሆኑም በኢትዮጵያ የአንድ ሰው የወተት ፍጆታ በዓመት 19 ሊትር ብቻ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ። ይህ ደግሞ ከሌሎች አገራት ጋር ሲነፃፀር ሰዎች ከሚያስፈልጋቸው የወተት መጠን እጅግ በጣም አነስተኛው እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ከሰው ልጆች ዕድገት፣ ደህንነትና ጤንነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘው ወተት በተለይም ለሕጻናት ዋነኛ ምግብ ሆኖ ያገለግላል። ከሕጻናት ባለፈም ወጣትም ሆነ አዛውንት ለሁሉም ሰው ገደብ በሌለው መጠን እንዲጠጡትና ከምግብ ይዘቱም ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ ይመከራል። ወተት ከፍተኛ መጠን ያላቸውን የካልሲየም እና የፖታስየም ማዕድናትን እንዲሁም ቫይታሚን ዲን የያዘ በመሆኑ ሁሉም ሰው ቢያንስ በቀን አንድ ብርጭቆ ወተት እንዲጠጣ ይመከራል።

ታዲያ ይህ ፍላጎቱና አቅርቦቱ አልጣጣም ያለው የወተት ምርት በአሁን ወቅት ከእጥረቱ ባለፈ የዋጋው መናር እስከ ሶስት ዓመት ወተት ብቻ መመገብ ያለባቸው ሕጻናት እንኳ ማግኘት እንዳይችሉ የወተት መሸጫ ዋጋው ትልቅ ችግር እንደሆነ ይነገራል። ታዲያ ከሰሞኑ በወተት ምርት ላይ እየታየ ስላለው የዋጋ መናር አንስተን ያነጋገርነው የቤት ለቤት ወተት አቅራቢ ለወተት ዋጋ መናር ምክንያቱ የመኖ መወደድ መሆኑን ይናገራል።

የቤት ለቤት ወተት አቅራቢው አቶ ጌታቸው አየለ፤ ከኦሮሚያ ክልል ሰበታ ከተማ አካባቢ የሚያመጣውን ወተት በመኖሪያ አቅራቢያው በሆነው ጀሞ ቁጥር አንድ፣ ቁጥር ሁለትና ቁጥር ሶስት ድረስ ሲያከፋፍል የቆየ ቢሆንም በአሁን ወቅት የከብቶቹ መኖ መወደድ በየጊዜው በወተት ዋጋ ላይ ጭማሪ እንዲያደርግ አስገድዶታል። ይህም ለሥራው እንቅፋት ከመሆን ባለፈ ደንበኞቹን ሊያሳጣው እንደሆነ ይናገራል።

አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥም ሁለት ጊዜ ጭማሪ ለማድረግ መገደዱን የተናገረው አቶ ጌታቸው፤ በቅርቡ የአንድ ሊትር ወተት ዋጋ 30 ብር የነበረና በአሁን ወቅት ግን 60 ብር ለማድረግ መገደዱን ያስረዳል። በዚህ ምክንያትም አብዛኛውን ደንበኛ በወር ኮንትራት ገብቶ ሲወስድ የነበረ ውሉን እያቋረጠ ነው በማለት አጠቃላይ የኑሮ ውድነቱ እያደረሰ ያለው ጫና በተለይም የወተት ዋጋ መወደድና የምርት እጥረት መኖሩ ከባድ ፈተና መሆኑን ያስረዳል።

ቤት ለቤት ለሕጻናቱ ከሚከፋፈለው ወተት በተጨማሪ በየሱቁና ሱፐርማርኬቶች አካባቢ ለገበያ የሚቀርበው ወተትም እንዲሁ ከፍተኛ የሚባል ጭማሪ ያሳየ መሆኑን መመልከት ችለናል። ማማ፣ ሾላ፣ ሎሚ፣ ሐርሜና ወዘተ መጠሪያ ያላቸው ፓስቸራይዝድ የሆኑት የወተት አይነቶች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ 20 ብር ይሸጡ የነበረ ቢሆንም የፋሲካ ጾም ከተፈታ ወዲህ ግን ማንኛውም የላስቲክ ወተት ዋጋ ከ28 እስከ 30 ብር እየተሸጠ መሆኑን ማረጋገጥ ችለናል።

ቀድሞም የአቅርቦትና ፍላጎት ክፍተት ያለበት የወተት ልማት በአሁን ወቅት ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ጭማሪ የታየበት ከመኖ አቅርቦት ጋር በተያያዘ ስለመሆኑ ብዙዎች ያነሳሉ። እርግጥ ነው የወተት ዘርፉን ምርታማና ውጤታማ ለማድረግ የእንስሳት መኖን ማሻሻል ወሳኝ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አንዱ ስለመሆኑ ይታመናል። የመኖ ስትራቴጂ መኖር ያለበት ስለመሆኑም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች አጽንኦት ሰጥተው ሲናገሩ ይደመጣል። በቂና የተመጣጠነ የእንስሳት መኖ በአገሪቷ መልማትና መስፋፋት እንዳልቻለና ይህን ማስፋትና ማልማትም የግድ ነው ይላሉ።

ከመኖ በተጨማሪ የእንስሳቱን ዝርያ ማሻሻልም ወሳኝ እንደመሆኑ የተሻሻሉ ዝርያዎችን በአገሪቱ በማምጣት እንዲሁም የእንስሳቱን ጤና በመጠበቅ በወተት ምርት ላይ ውጤት ለማምጣት መሠራት ያለበት መሆኑ ይታመናል። ታዲያ በዘርፉ ምን እየተሠራ ነው? በአሁን ወቅት ያለው የወተት ዋጋ መናርስ ከምን የመጣ ነው? መፍትሔውስ? ስንል ላነሳነው ጥያቄ በግብርና ሚኒስቴር የወተት ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ አስመላሽ በርሄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

በወተት ገበያ ላይ አሁን እየታየ ያለው የዋጋ ውድነት

**የወተት ዋጋ አነጋጋሪ ሆኗል፤**

የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩትም በዋናነት የወተት አምራቾች ለወተት ልማት ግብዓት የሚጠቀሟቸው ምርቶች መካከል የመኖ ዋጋ መወደድ በዋናነት የሚጠቀስ ነው።

የመኖ መወደድ በአሁን ወቅት በወተት ዋጋ ላይ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ጭማሪ እንዲከሰት አድርጓል። ይሁንና የግብርና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከዚህ ቀደም በወተት ልማትና ግብይት የሚታዩ መሰል ችግሮችን መቅረፍ የሚያስችል ስትራቴጂ ቀርጾ የተለያዩ ሥራዎችን መሥራት ጀምሯል። ከእነዚህም መካከል የመኖ አቅርቦት አንዱ ነው።

ለከብቶች አስፈላጊ የሆነውን መኖ በጥራትና በስፋት ማቅረብ እንዲቻል በተለይም ከተረፈ ምርት ጋር ተያይዞ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ከፍተኛ መጠን ያለው ተረፈ ምርት የሚገኝባቸውን አካባቢዎች በመለየት የመኖ አቅርቦቱን ማሻሻል እንዲቻልና ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት እየተደረገ ሲሆን ለአብነትም በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራና ሲዳማ ክልሎች ላይ ሥራው ተጀምሯል።

ሥራውም ከአራቱም ክልሎች የተውጣጡ ባለሙያዎች በማሰልጠንና ከግብርና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ባለሙያዎች ጋር በማቀናጀት በየወረዳው ካሉ አርብቶ አደሮች ጋር መኖን የማሻሻል ተግባር እየተከናወነ ይገኛል። መኖን በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል እንዲሁም ሌሎች በዘርፉ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ እየተሠራ መሆኑን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤

የመኖ እጥረትን ለማሻሻልና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከተጀመረው ሥራ በተጨማሪ በቅርቡ የወተት ዋጋ በገበያው ላይ ከፍተኛ ጭማሪ በማሳየቱ ምክንያት ከኅብረተሰቡ እየተሰሙ ያሉ ሮሮዎች ስለመኖራቸው አስታውሰው በዘርፉ ከተሰማሩ አካላትም የተለያዩ ጥያቄዎች እንደቀረቡላቸው ተናግረዋል። ጥያቄውንና የኅብረተሰቡን ሮሮ ተከትሎም ችግሩን ለመለየትና መፍትሔ ለማፈላለግ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየተሠራ መሆኑን ዳይሬክተሩ አመላክተዋል።

አጠቃላይ ለወተት ማምረት ከሚወጣው ወጪ 60 በመቶ የሚሆነው ለመኖ የሚወጣ ወጪ እንደሆነ በጥናት የተረጋገጠ መረጃ ያሳያል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በጥናት የተረጋገጠ ባይሆንም በአሁን ወቅት ደግሞ መኖ ከ60 በመቶ በላይ ወጪ የሚጠይቅ ስለመሆኑ እየተነገረ ነው። በመሆኑም በአሁን ወቅት የመኖ ዋጋ በከፍተኛ መጠን መጨመር ጥያቄ የሆነባቸው ወተት አምራች የሆኑ ማኅበራት ወደ ግብርና ሚኒስቴር የወተት ልማት ዳይሬክቶሬት ጋር እየመጡ ሲሆን ዳይሬክቶሬቱም አማራጭ ያላቸውን የመፍትሔ አቅጣጫዎች እያስቀመጠ መሆኑን አስረድተዋል።

በተለይም ባለሃብቱ ስንዴን በሰፊው እያለማ ከራሱ አልፎ ለሌሎችም መትረፍ የሚችልበትን መንገድ ለማመቻቸት እየተሠራ ነው። በከተማና ከተማ ዳርቻ የሚገኙ ወተት አምራቾች በዋናነት የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶችን ለወተት ላሞች መኖ የሚጠቀሙ ሲሆን፤ የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶችም በተለያየ መንገድ እጥረት እያጋጠማቸው ይገኛል።

የተረፈ ምርቱ እጥረትም በአገር ውስጥ የሚገኙ የዘይትና የዱቄት ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ምርት እጥረት እያጋጠመው መሆኑ ነው። ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ምርት እጥረት ካጋጠመው የሚገኘውም ተረፈ ምርት እንዲሁ የሚቀንስ በመሆኑ መኖ መሆን በሚችለው ተረፈ ምርት ላይም እጥረት የተከሰተና እጥረቱም የዋጋ ንረት እንዲከሰት አድርጓል።

በአገር ውስጥ ከሚመረቱና ፕሮሰስ ከሚደረጉ ምርቶች መካከል ለእንስሳት መኖ የዘይትና የዱቄት ፋብሪካዎች ቀዳሚዎች ናቸው። ይሁንና በአሁን ወቅት ካለው ችግር በመነሳት የገጠመውን የመኖ እጥረት ለመቀነስ በተለይም ቢራ ፋብሪካዎች ከሚያመርቱት ምርት የሚገኘውን ተረፈ ምርት ከደላላ ውጭ በሆነ መንገድ መጠቀም እንዲቻል እየተሠራ እንደሆነም ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

የመኖ ዋጋ መናር አጠቃላይ በአገሪቱ ካለው የኑሮ ውድነት ጋር የተያያዘ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ፋብሪካዎች በሚያመርቱት ምርት ላይ የሚጨምርባቸውን የተለያዩ ግብዓቶች ፣ የትራንስፖርት ጭማሪ እንዲሁም የሠራተኛ ወጪን በመደመር በተረፈ ምርት ላይ ጭማሪ ማድረጋቸው እንዳለ ሆኖ በመሐል ያለው ደላላ የዋጋ ንረቱን እያባባሰ ስለመሆኑ አንስተዋል።

በመሆኑም በፋብሪካዎችና በወተት አምራች ማኅበራቱ መካከል ያለውን ደላላ ከጨዋታ ውጭ በማድረግ ተረፈ ምርቱን ማኅበራቱ በቀጥታ ከፋብሪካዎቹ ማግኘት የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እየተሠራ ነው። ለዚህም ትልቁን ድርሻ መውሰድ ያለባቸው ወተት አምራች ማኅበራቶቹ ናቸው። ማኅበራቱ ገፍተው በመሄድ ከፋብሪካዎች ጋር ቀጥታ ግንኙነት መፍጠር አለባቸው። በዚህ ጊዜ ተረፈ ምርቱን ከደላላ ውጭ በሆነ መንገድ ማግኘት ይችላሉ። ይህን አማራጭ መጠቀም እንዲችሉም ዳይሬክቶሬቱ የማመቻቸት ሥራ እየሠራ ሲሆን መንግሥትም ገበያውን የማረጋጋት ሥራ መሥራት ያለበት እንደሆነ ተናግረዋል።

አጠቃላይ በሃገሪቱ የሚቀርበው የወተት ምርት ከአነስተኛ አርሶ አደሮች አካባቢ እንደሆነ ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ በእነዚህ አነስተኛ አርሶ አደሮች እጅ የሚገኙት የወተት ላሞች ደግሞ ከአምስት ያልበለጡ ናቸው። እነሱም ምርታማነታቸው ዝቅተኛ ነው ይላሉ። የወተት ላሞቹ ሃገረሰብ ዝርያዎችን የያዙ በመሆናቸው ቢበዛ በቀን እስከ አንድ ነጥብ አራት ሊትር ወተት የሚሰጡ ናቸው። ነገር ግን በአሁን ወቅት በማዳቀል ቴክኖሎጂ የሚይዟቸው ዝርያዎች ያሉ ሲሆን እነዚህም በቀን እስከ ስድስት ሊትር ወተት መስጠት የሚችሉ ናቸው።

ይሁንና ከእነዚህ አርሶ አደሮች የሚገኘው የወተት ምርትም ሙሉ ለሙሉ ወደ መደበኛ ገበያው ወይም ወተት መሰብሰቢያ ጣቢያ እየገባ አይደለም። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች የሚጠቀሱ ሲሆን የወተት ገበያው በመደበኛ የገበያ ሥርዓት እየተመራ አለመሆኑ አንዱ ምክንያት መሆኑን ዳይሬክተሩ አንስተው፤ የወተት ግብይት ሥርዓቱ ጠንካራ አለመሆን አንዱ ችግር ነው ብለዋል።

የወተት ምርቱ ወደ ገበያ የሚወጣው በአብዛኛው መደበኛ ባልሆነ የገበያ ሥርዓት በመሆኑ ቁጥጥርና ክትትል የለውም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ቁጥጥርና ክትትል በሌለው ሁኔታ የሚመጣ ምርት ደግሞ የዋጋም ሆነ የጥራት ቁጥጥር አይኖረውም። ስለዚህ በአሁን ወቅትም የሚታየው የዋጋም ሆነ የጥራት ችግር ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመጣ ነው።

በሃገሪቱ በዋናነት ወተት የማምረት አቅም አላቸው ተብለው የተለዩ ክልሎች አሉ። በተለይም በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም፣ ምዕራብ ጎንደር፣ ደቡብ ወሎ፣ ደብረብርሃንና ሰሜን ሸዋ ሲሆኑ፤ በኦሮሚያ ክልል ሰላሌ፣ ሻሸመኔና በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ደግሞ አዳማና አሰላ አካባቢ የወተት ምርት ስለመኖሩ ተለይቷል። በሲዳማ ክልልም እንዲሁ ሀዋሳ ዙሪያና ዲላ የሚገኝ ሲሆን በደቡብ ክልል ደግሞ ከምባታ ጠንባሮ አካባቢ ከፍተኛ አቅም ያላቸው መሆናቸው ተለይቶ ከዝርያ ማሻሻያ ጋር ተያይዞ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠራ ነው።

በእነዚህ አካባቢዎች የሚሠራው ዝርያን የማሻሻል ሥራ በቀጣይ ውጤት ማምጣት የሚችል ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በተለይም መንግሥት ተነሳሽነቱን ወስዶ በተለያዩ የምርምር ማዕከሎችና ራንቾች ላይ የቦረናና የፎገራ ከብቶችን በማስገባት የማዳቀል ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

መንግሥት ከሚሠራው ሥራ በተጨማሪ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የግሉ ዘርፍም በስፋት ገብቶ መሳተፍ ያለበት መሆኑን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ከመንግሥት በተጨማሪ በተለይም ከዝርያ ማሻሻያ ጋር ተያይዞ የማዳቀል ሥራ ላይ እንዲሁም ብዜት ላይ የግል ባለሃብቱ ትልቅ ድርሻ ያለው ነውና ሊሳተፍ ይገባል። የግል ባለሃብቱ በዘርፉ መሳተፍ እንዲችል በመንግሥት በኩል ከመሬት አቅርቦት ጀምሮ የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን በማሟላት የሚወሰዱ እርምጃዎች እንዳሉና የተጀመሩት ሥራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በመጨረሻም ከመኖ ጋር ተያይዞ የመኖ አቅርቦትን በስፋት ለማምረት ከፋብሪካዎች በተጨማሪ የወተት አምራች ማኅበራቱ በራሳቸው መሬት በመጠየቅ መኖ አምርተው ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች መትረፍ የሚችሉበትን መንገድ በመከተል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚቻልበት አጋጣሚ መኖሩን በመግለጽ ሀሳባቸውን ቋጭተዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የሳይንስ ቃላትና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማር

**ዋለልኝ አየለ**

ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማሪያ መጻሕፍትን ከተማሪዎች እየተቀበልኩ አያለሁ። በተለይም የአንደኛ ደረጃ (እስከ 8ኛ ክፍል) ሳይንስ በአማርኛ የተማርኩባቸው የሳይንስ ቃላት ይታሰቡኛል። ለሳይንስ ትምህርቱ ሲባል የተፈጠሩ የአማርኛ ቃላት ይስቡኛል።

ባለፈው ሐሙስ ከሰዓት የሆነ የቴሌቪዥን ጣቢያን ለማግኘት ቻናል እያቀያየርኩ ነበር፤ በአጋጣሚም በአንድ የቴሌቪዥን ጣቢያ ትምህርት በቴሌቪዥን ሲተላለፍ አገኘሁ። በቴሌቪዥኑ የሳይንስ ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ እየተላለፈ ነበር፤ ሪሞቱን አስቀምጬእየተሰራጨ ያለውን ትምህርት መከታተል ጀመርኩ። ለካስ ሊያልቅ አካባቢ ነበርና የደረስኩበት ትምህርቱ የሳይንስ መሆኑን እንጂ የትኛው የሳይንስ ትምህርት ዓይነት እና የስንተኛ ክፍል እንደሆነ አላየሁም። ከማስታውሳቸው የሳይንስ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦች ተነስቼም የ7ኛ ክፍል ፊዚክስ ነው ስል ገመትኩ።

በትምህርቱ ውስጥ ከአሥራ ምናምን ዓመታት በፊት የማውቃቸውን የአማርኛ የሳይንስ ቃላት ስሰማ አዘጋጆቹን አመሰገንኳቸው። ምክንያቱም በአንደኛ ደረጃ መማሪያ መጻሕፍት ላይ በአንዳንድ የሳይንስ ትምህርቶች የሳይንስ የእንግሊዝኛ ቃላት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተተርጉመው ይሠራባቸው የነበረበት ሁኔታ ቀረ ወይ የሚያሰኝ ሁኔታን እንድታዘብ አረገኝ።

በሃገራችንም ይህን አሠራር ክልሎች በተለያየ መልኩ እየተገበሩት ይገኛሉ። በኦሮሚያ ክልል እስከ 8ኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጠው በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንደነበር አውቃለሁ (አሁን የተቀየረ ነገር ከሌለ)፤ በአማራ ክልልና አዲስ አበባ ግን 7ኛና 8ኛ ክፍል ላይ ትምህርት የሚሰጠው በእንግሊዘኛ ነው። አማራ ክልል የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል ትምህርት መስጫው ወደ አፍ መፍቻ ይመለሳል ሲባል ነበር። ለማንኛውም የክልሎች የትምህርት ፖሊሲ ምን ላይ እንዳለ ለጊዜው ሙሉ መረጃ ስለሚፈልግ እሱን እንለፈው። ዋናው ነገር ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲማሩ መደረጉ መሰጠት እንዳለበት ይታመናል፤ ትክክልም ነው።

ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከወጣሁ ጊዜ ጀምሮ የሚቀየሩ የመማሪያ መጻሕፍትን ከተማሪዎች እየተቀበልኩ አያለሁ። 2008 ይሁን 2009 አካባቢ በዚህ ጉዳይ ላይ ትዝብት መጻፌን አስታውሳለሁ። የ4ኛ፣ 5ኛና 6ኛ ክፍል የሳይንስ መማሪያ መጽሐፎችን ከልጆች ላይ እየተቀበልኩ ሳይ እነዚያ እኔ የተማርኩባቸው ቃላት የሉም። ይህ የሆነው እንግዲህ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ለሆኑ ተማሪዎች ነው።

የመማሪያ መጽሐፉ ለስሙ በአማርኛ ነው የተዘጋጀው። የሳይንስ ቃላቱን ለተመለከተ ግን የተጻፈበት ፊደል ነው እንጂ አማርኛ፤ ቃላቱ የእንግሊዘኛ ናቸው። ቀደም ሲል በነበረው ግን በአማርኛ ቃላት ይጻፍና አንዳንድ ቦታ ላይ እንግሊዝኛው በቅንፍ ውስጥ ይሆናል። ይህ ሲሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የእንግሊዘኛ አቻውን እያወቁት ይሄዳሉ ማለት ነው። በመማሪያ መጽሐፉ ጀርባ ደግሞ ሙዳዬ ቃላት(Glossary) ተብሎ ይቀመጣል። ሙዳዬ ቃላቱ መዝገበ ቃላት ማለት ነው። የአማርኛ ቃላትን በእንግሊዝኛ የሚፈታ። እንግሊዝኛውንም በዚያ ነበር የምናውቀው። እንደ መምህራኑ ብቃት ደግሞ በአማርኛ እያስተማሩ የእንግሊዘኛ ቃላቱንም ያለማምዱን ነበር።

አሁን እየታዘብኩ ያለሁት ግን በአማርኛ ፊደል የእንግሊዝኛው ቃል /በላቲን ፊደል ደግሞ የእንግሊዝኛው ቃል/ እየተጻፈ ያለበትን ሁኔታ ነው። ለምሳሌ የምግብ ሥርዓተ ልመት (digestive system) መባል የነበረበት «ዳይጀስቲቭ ሲስተም( digestive system)» ተብሎ ይጻፋል። ይህ አገላለጽ ቦታ ከማባከን ውጭ ምንም ጥቅም የለውም ማለት ነው።

የትምህርት ጥራት ጉዳይ በየጊዜው ሲነሳ የቆየ ቢሆንም፣ የመማሪያ መጻሕፍት የሚጻፉበት ቋንቋ ጉዳይ ሆኖ ሲያከራክር ብዙም አይታይም፤ አልፎ አልፎ ብቻ በባህልና ስፖርት (በቀድሞው ባህልና ቱሪዝም) ሚኒስቴር «የአፍ መፍቻ ቋንቋ» እየተባለ ውይይቶች ይደረጋሉ።

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሳይንስ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ አለመሆኑ ከፍተኛ ጉዳት እንዳለው ይታመናል። ታችኛው የክፍል ደረጃ ላይ ደግሞ ሳይንሱ የአካባቢ ሳይንስ በሚል ነው የሚሰጠው። ሳይንስ ተፈጥሮ ነው፤ ተፈጥሮን ማወቅ የምንጀምረው ከአካባቢያችን ተነስተን ነው፤ አካባቢያችንን የምናውቀው ደግሞ በቋንቋ ነው። በአካባቢያችን ያሉ ነገሮችን አሳምሮ የሚገልጻቸው እነዚያ ተፈጥሮዎች የሚጠሩበት የአካባቢው ቋንቋ ነው። ሕጻናት የተክልና፣ የእንስሳት አይነቶችን፣ የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚያውቁት ከአካባቢያቸው ነው፤ የሚያውቁት ደግሞ በአካባቢያቸው በሚነገረው ቋንቋ ነው።

በአማርኛ የማውቃቸው የሳይንስ ቃላት ጽንሰ ሀሳቡ እንዲገባኝ ያደርጉኛል። መጀመሪያ በአማርኛ ካወቅኳቸው በኋላ ነው እንግሊዝኛው የሚገባኝ። አለበለዚያ መሸምደድ ብቻ ነው የሚሆነው። የአማርኛውን ቃል ከቤተሰብ ጀምሮ በአካባቢዬ ሲነገር አውቀዋለሁ፤ እንግሊዘኛውን ግን ያየሁት መማሪያ መጽሐፉ ላይ ብቻ ነው፤ ስለዚህ ድርጊት ገላጭ አይሆንም። ጽንሰ ሀሳቡ ገላጭ የሚሆነው እንግሊዘኛን በአፍ መፍቻነት ጭምር ካወቁት ወይም ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች በእንግሊዘኛ ከሆኑ ነው። የእሳት ዳር ጨዋታዎች ሁሉ በእንግሊዘኛ ከሆኑ ነው።

የሳይንስ ቃላት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መገለጻቸው የዚያን ቃል ትርጉም በቀላሉ ለማወቅ ያግዛል። ለምሳሌ፤ በሳይንሱ ደም መላሽ እና ደም ወሳጅ የሚባሉ የደም ቧንቧ አይነቶች አሉ። ወሳጅ የሚለውም ሆነ መላሽ የሚለው ቃል ምንን እንደሚገልጽ አፉን በአማርኛ የፈታ ለመረዳት ብዙም አይቸገርም፤ ለማስረዳትም አያስቸግርም። ከቃሉ ጋር ከሕጻንነቱ ጀምሮ ተላምዷል። ስለዚህ «ደምን ከልብ ወደ ተለያዩ የሰውነት ክፍሎች የሚወስድ የደም ቧንቧ ምን ይባላል?» ተብሎ ቢጠየቅ፤ «ወሳጅ» የሚለው ቃል ድርጊቱን ስለሚገልጽ «ደም ወሳጅ» ብሎ ይመልሳል ማለት ነው።

«የሰውነት ሕዋሳት ተጠቅመውበት የቆሸሸውን ደም ወደ ልብ የሚመልስ የደም ቧንቧ ምን ይባላል?» ቢባል «መላሽ» የሚለው ቃል ድርጊቱን ስለሚገልጽ «ደም መላሽ» ብሎ ይመልሳል ማለት ነው። Arteries እና Veins የሚሉት የእንግሊዘኛ ቃላት ግን ለ4ኛና 5ኛ ክፍል ተማሪ የአማርኛውን ያህል ሊገልጹለት አይችሉም። ጽንሰ ሀሳቡን ሳይሆን የሚይዘው ለሸምደዳ ነው የሚታገል።

ለዚህ ሀሳብ መነሻ የሆነኝ ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት በሃገራችን አንድ የቴሌቪዥን ጣቢያ ሲተላለፍ በነበረ የትምህርት በቴሌቪዥን ስርጭት የተመለከትኳቸው የሳይንስ ትምህርት የአማርኛ ቃላት ናቸው። በትምህርቱ ውስጥ «ፅብረቃ፣ የብርሃን ሀመልማሎ...» የሚሉ ቃላት አሉ። እነዚህ ቃላት ትርጉምን መግለጽ ብቻ ሳይሆን ስነ ጽሑፋዊ ውበትም አላቸው። ማንፀባረቅ ከሚለው ቃል ጽብረቃ የሚል ድርጊት አመልካች ቃል ይፈጠራል ማለት ነው። ሂደቱ ጽብረቃ ይባላል። በተለይ የስነ ሕይወት (ባዮሎጂ) ቃላት በአፍ መፍቻ ሲሆኑ ደግሞ የበለጠ ገላጭ ይሆናሉና ተማሪዎች ጽንሰ ሀሳብን ይይዙ ዘንድ ፋይዳቸው ከፍተኛ ነው።

የተፈጥሮ ሳይንስን ብቻ አይደለም፤ የማኅበራዊ ሳይንስም በአፍ መፍቻ ሲሆን ተማሪዎች ታሪክ፣ ስነ ዜጋና ስነ ምግባር በቀላሉ እንዲገባቸው ያደርጋል። የታሪክ እና የስነ ዜጋ ይዘቶች በተዘዋዋሪ በቤት ውስጥም የሚወሩ እንደመሆናቸው ቃላቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መገለጻቸው በሕይወት ገጠመኝ ውስጥ የሚያውቁትን መደበኛው ትምህርት ውስጥ እንዲያገኙት ለማድረግ ያስችላሉ።

ስለትምህርት ጥራት ሲታሰብ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ነገርም ተያይዞ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የመማሪያ መጻሕፍት በተገቢው ቋንቋ ባይጽፉ እንኳን መምህራን ግልጽ አድርገው ማስተማር አለባቸው። በዚህ በኩል ከመማሪያ መጻሕፍቱ ይልቅ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ትምህርቶች የተሻለ ሁኔታ ይታያል።

አንደኛ ደረጃ ላይ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰጠት ያለበት መሆኑ ታምኖበት እየተሠራበት እንደመሆኑ ሁሉ፣ ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍትም በሚገባ ቋንቋ መጻፍ አለባቸው፤ መጻሕፍቱ ላይ ክፍተት ካለ ደግሞ የሚመለከታቸው አካላት መሙላትና ማሻሻል ላይ ትኩረት አርገው መሥራት ይኖርባቸዋል፤ ይህ እስኪሆን ደግሞ መምህራን በማስተማር ዘዴ ተማሪዎቹን በመርዳት ሊያሳውቁ ይገባል!

# ዓለም አቀፍ



## በተባበሩት መንግሥታት የሚመራው የሱዳን ድርድር ተቃውሞ ገጠመው

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሚመራው የሱዳን የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁለተኛ ዙር ድርድር በዛሬው ዕለት እንዲጀመር እቅድ የተያዘለት ቢሆንም መከፋፈሎች አጋጥመዋል።

በጥቅምት ወር የተካሄደውን ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ተከትሎ የተፈጠረውን የፖለቲካ ቀውስ ለመፍታት ባለመው ድርድር ላይ እንደማይሳተፉ በርካታ ፓርቲዎች እየገለጹ ይገኛል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የአፍሪካ ኅብረት እና የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) ጥምረት በአገሪቱ ያሉትን ወታደራዊ ኃይል፣ የዲሞክራሲ ተሟጋቾች እና የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማደራደር ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

በድርድሩ አንገኝም ካሉት መካከል የሱዳን ባለሙያዎች ማኅበር (ኤስፒኤ)፣ የሱዳን ኮሚኒስት ፓርቲ (ኤስሲፒ) እና የሱዳን ኮንግረስ ፓርቲ (ኤስኮፒ) ይገኙበታል።አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውይይቱን “ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥቱን ሕጋዊ ለማድረግ የተደረገ ሙከራ ነው” ሲሉ ሌሎች ደግሞ በይፋ አልተጋበዝንም ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

አሜሪካ ሁሉም የሃገሪቱ ሲቪል እና ወታደራዊ አካላት በተባበሩት መንግሥታት የሚመራውን ድርድር በመደገፍና ይህንንም ሂደት በመጠቀም ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን እና ብሔራዊ መረጋጋትን እንዲያመጡ አሳስባለች።” በሱዳን ዲሞክራሲያዊ ሽግግር ለማምጣትና የሲቪል አመራሩን ወደነበረበት ለመመለስ እየተደረገ ላለው ጥምር ጥረት ጠንካራ ድጋፍ ታደርጋለች” ብሏል ከአሜሪካ በኩል የተሰጠው መግለጫ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከ100 የሚበልጡ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ የወጣቶች እና የሴቶች ቡድኖች የሱዳንን ሉዓላዊነት እንዲከበር የሚጠይቅ ሰነድ ትናንት ሰኞ ፈርመዋል።በዋናነት የወታደራዊ ኃይሉ ደጋፊ የሆኑት እነዚህ ቡድኖች በሃገሪቱ የውስጥ ጉዳይ ላይ “የውጭ ጣልቃ ገብነት” እንደማይቀበሉ እና አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሾሙ ጠይቀዋል።

## ሕንድ ውስጥ አካል ጉዳተኛው ታዳጊ ወደ አውሮፕላን እንዳይገባ መከልከሉ ቁጣን አስነሳ



ሕንድ ውስጥ አንድ አካል ጉዳተኛ ታዳጊ ወደ አውሮፕላን እንዳይገባ መከልከሉን ተከትሎ የሃገሪቱ አቪዬሽን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ጉዳዩን እየመረመረው እንደሆነ አስታውቋል።በሃገር ውስጥ ብቻ በረራዎችን የሚያደርገው አየር መንገዱ ታዳጊው ለራሱና ለሌሎች ተሳፋሪዎች ስጋት ስለሚፈጥር ወደ አውሮፕላኑ መግባት እንደማይችል ለቤተሰቦቹ ገልጾ ነበር።

ይህ ክስተት ታዲያ ሕንድ ውስጥ ትልቅ መነጋገሪያ መሆን ብቻ ሳይሆን በርካቶችን ያስቆጣ ሆኗል።የሕንድ ዜጎችም በሃገራቸው ያለውን መሰል የማግለልና መድልኦ ሥርዓት በመቃወም ድምጻቸውን እያሰሙ ነው። ኢንዲጎ የተሰኘው አየር መንገድ የቀረበበትን ክስ በማስተባበል እንዲያውም ሁሉንም አካታች የሆነ ሥርዓት የሚከተል ድርጅት እንደሆነ ገልጿል።

የሕንድ አቪዬሽን ሚኒስትሩ ጆይቲራዲትያ ሲንዲያ በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን ሲሰጡ ”ጉዳዩን በደንብ እየመረመርነው ነው፤ ተገቢውም እርምጃ ይወሰዳል” ብለዋል።”መሰል ተግባራትን የሚታገስ ሕግ የለንም። ማንኛውም አይነት የሰው ልጅ በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ሊያልፍ አይገባም” ብለዋል በትዊተር ገጻቸው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት በተጨማሪም አየር መንገዱ በዕለቱ ምን እንደተከሰተ የሚገልጽ ሪፖርት እንዲያስገባም ጠይቀዋል።ታዳጊው ወደ አውሮፕላኑ እንዳይገባ የተከለከለው ባሳለፍነው ቅዳሜ ሲሆን በቦታው የነበረች ማኒሻ ጉፕታ የተባለች ተሳፋሪ ሁኔታውን በማስመልከት በፌስቡክ ገጿ ላይ ጉዳዩን በተመለከተ መጻፏን ተከትሎ ነው ለሕዝብ ይፋ የሆነው።

ሚኒሻ ጉፕታ እንዳለችው ታዳጊው በተፈጠረው ነገር ተደናግጦና አዝኖ ነበር ብላለች። ”የአየር መንገዱን ፍተሻ አልፎ ወደ አውሮፕላን ለመግባት በተቃረበበት ወቅት አትገባም ሲባል በጣም ደንግጦ፣ ተጨንቆና ግራ ተጋብቶ ነበር። አጠገቡ የነበሩት ቤተሰቦቹ በተቻላቸው መጠን ለማረጋጋት ሲሞክሩና ሲያጽናኑት ነበር”

”የአየር መንገዱ ሠራተኞች ስልጣናቸውን ለማሳየት እየሞከሩ ይመስል ነበር። የበረራ አስተናጋጆቹ ሁሉም ታዳጊው መግባት እንደማይችል በተደጋጋሚ ይናገሩ ነበር። ለተጓዦች ስጋት እንደሆነ በመግለጽ ነበር ታዳጊውና ቤተሰቦቹን ሲከለክሏቸው የነበረው”

ሌሎች ተሳፋሪዎችም አካል ጉዳተኛው ታዳጊም ሆነ ቤተሰቦቹ ወደ አውሮፕላኑ ቢገቡ ቅር እንደማይላቸው ገልጸውም ነበር። እንደውም በአውሮፕላኑ ውስጥ የነበሩ የሕክምና ባለሙያዎች ተገቢውን ክትትል እንደሚያደርጉለትና ምንም ችግር እንደማይፈጠር ቢገልጹም የአየር መንገዱ ሠራተኞች ግን በአቋማቸው ጸንተዋል።

ማኒሻ ጉፕታ ክስተቱን ተከትሎ በፌስቡክ ገጿ ላይ ያሰፈረችው መልዕክትም በመላው ሕንድ ትልቅ መነጋገሪያ መሆን ችሏል። በርካቶችም አየር መንገዱ ላይ ተቃውሟቸውንና ቁጣቸውን እየገለጹ ነው። መንግሥትም ተገቢውን ምርመራ አድርጎ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስድ ጠይቀዋል።

ኢንዲጎ አየር መንገድ በበኩሉ የተሳፋሪዎቹን ደህንነት ለመጠበቅ የተቻለውን ሁሉ እንደሚያደርግና በዚህ አጋጣሚ እንግልት የደረሰበትን ቤተሰብ ለአንድ ቀን በሆቴል እንዲቆዩ ማድረጉን ገልጿል። አክሎም ታዳጊውና ቤተሰቦቹ በቀጣዩ ጠዋት ወደሚፈልጉበት ቦታ እንዲሄዱ ማድረጉንም አስታውቋል።

”በተፈጠረው ነገር በጣም አዝነናል። ኢንዲጎ አየር መንገድ ሁሉንም አካታች ድርጅት እንደሆነ ያምናል። ለሠራተኞቹም ሆነ ለተሳፋሪዎቹ ምቹ አካባቢ ነው” ብሏል።

ሕንድ ውስጥ 26 ሚሊዮን አካላዊና ጉዳትና ነገሮችን በቀላሉ የመረዳት ችግር (learning disabilities) ያለባቸው ዜጎች የሚገኙ ሲሆን ስለ ችግሮቹ ያለው ግንዛቤና ለነሱ የሚሆን መሠረተ ልማት ግን በጣም ዝቅተኛ ነው። በሌላ በኩል እነዚህ ሰዎች የተለያዩ አይነት መገለልና መድሎ እንደሚደርስባቸው በጉዳዩ ላይ ማኅበረሰብ የማንቃት ሥራ የሚያከናውኑ ሰዎች በተደጋጋሚ እንደሚገልጹ ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ደበበ ሰይፉ - ሁስገቡ የሥነጽሑፍ ባለሙያ

**አንተነህ ቸሬ**

ለዛሬ ገጣሚ፣ ፀሐፊ ተውኔት፣ ደራሲ፣ ሃያሲ፣ ተርጓሚ፣ መምህር፣ የሥነጽሑፍ ተመራማሪና የገዘፈ ሰብዕና ባለቤት የሆነው ደበበ ሰይፉ ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ፣ ተውኔትና ሌሎች የኪነጥበብ ዘርፎች ስላበረከታቸው አስተዋፅኦዎች በጥቂቱ እንመለከታለን።

ደበበ ሰይፉ ሐምሌ 5 ቀን 1942 ዓ.ም ከበጅሮንድ ሰይፉ አንተንይሥጠኝ እና ከወይዘሮ የማርያምወርቅ አስፋው ባለውለታው፣ የማንነቱ መገኛ፣ የዕውቀቱ መፍለቂያና መድመቂያ መሆኗን በግጥሙ ባሞካሸትና በደቡቡ የአገራችን ክፍል በምትገኘው ይርጋለም ከተማ ተወለደ። ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ልዩ የማንበብ ፍቅር ነበረው። ፊደል የቆጠረው በቄስ ትምህርት ቤት ነው። የትምህርት አቀባበሉ አስደናቂ ስለነበር መምህሩ የቤተ ክህነት አገልጋይ እንዲሆን ፈልገው ነበር። ይሁን እንጂ አባቱ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት እንዲገባ አደረጉት። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ይርጋለም ከተማ ውስጥ በሚገኘው ራስ ደስታ ትምህርት ቤት አጠናቀቀ።


በመቀጠልም ወደ አዲስ አበባ በመዛወር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በኮከበ ጽባሕ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትምህርት ቤት ተማረ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናውን በማለፍ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ (የአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)ን ተቀላቀለ። ወደ ዩኒቨርሲቲው ሲገባ የቢዝነስ ትምህርት ክፍል ተማሪ ሆኖ ነበር። ይሁን እንጂ ደበበ የነፍሱ መሻት ሥነጽሑፍ እንጂ ቢዝነስ ስላልነበር የቢዝነስ ትምህርቱን ለአንድ ዓመት ያህል ከተማረ በኋላ ወደ ሥነጽሑፍ ትምህርት ተዛወረ። በ1965 ዓ.ም ከዩኒቨርሲቲው የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል በከፍተኛ ማዕረግ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመረቀ። ቀጥሎም በ23 ዓመቱ በዚያው በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሥነጽሑፍን ማስተማር ጀመረ። ከአምስት ዓመታት በኋላ ደግሞ በእንግሊዝኛ ሥነጽሑፍ (English Literature) የሁለተኛ ዲግሪውን እንደ ቀድሞው ሁሉ በከፍተኛ ማዕረግ ማጠናቀቅ ችሏል።

የትምህርት ክፍሉንና የጥናት መስኩን በተመለከተ የተሰሩ በርካታ ስራዎች እንደሚያሳዩት የጥናትና የምርምር ውጤቶች በስፋት መሠራት በመጀመራቸው እንደ ደበበ ሰይፉ ያሉ መምህራን በዚህ ትምህርት ክፍል ውስጥ መቀላቀል ሲጀምሩ የትምህርት ክፍሉም እየተነቃቃ፣ እያደገና እየተስፋፋ የመጣበት ዘመን ነበር። ደበበ የኢትዮጵያ የሥነጽሑፍ፤ በተለይም ዐቢይ የሥነጽሑፍ ዘርፍ የሆነው የሥነግጥም ታሪክንና በዚህ ታሪክ ውስጥ ደግሞ ኪነታዊ አስተዋፅኦአቸው ሰፊ የሆኑትን ታላላቅ ጸሐፊያንን ታሪክና የአጻጻፍ ቴክኒካቸውንም ጭምር እያጠና ማቅረብ ጀመረ። ያለፈው የጥበብ አሻራ ለመጪው ጥበብ የሚያቀብለውን መረጃ እያዛመደ ትውልድን በጥበብ ማስተሳሰር አንዱ ተግባሩ ነበር።

ደበበ በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ የታሪክ፣ የሥነግጥም፣ የትያትር፣ የፍልስፍና (በተለይም የእነ ማርክስን ፍልስፍና)፣ የፖለቲካ … ጽንሰ ሃሳቦችን ከጥንታዊ ሰነዶች ውስጥ እየፈተሸ በማውጣት ‹‹እንዲህ ነበር፣ እንዲህም ኖሯል፣ እንዲህም አ(ታ)ስቧል …›› እያለ በትውልድ መካከል የመሸጋገሪያ ድልድይ ሆኖ አገልግሏል።

ደበበ የተዋጣለት ገጣሚ ነበር። በአገጣጠም ችሎታው ውብ እና ማራኪነት የተነሳ ብዙዎች ‹‹ባለቅኔው ደበበ ሰይፉ›› እያሉ ይጠሩታል። ይህ በሥነግጥም ዓለም ውስጥ የተሰጠው ፀጋ ከሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ገዝፎ የሚነገርለት፤ የሚታወቅበትም ነው። ደበበ ሲነሳ ገጣሚነቱ አብሮ ብቅ የሚልለት የጥበብ ሰው ነው። እነዚህ የግጥም ትሩፋቶቹ በአንድ ላይ ተሰባስበው ‹‹የብርሃን ፍቅር›› በሚል ርዕስ ታትመዋል። ይቺ የሥነግጥም መጽሐፍ ደበበ ቀደም ሲል በተማሪነት እና በአስተማሪነት ዘመኑ ሲጽፋቸው የነበሩት ግጥሞች ተካትተው የሚገኙባት ድንቅ መጽሐፉ ነች።

ከዚህች መጽሐፉ በተጨማሪ በ1992 ዓ.ም፣ በሜጋ አሳታሚ ድርጅት አማካኝነት ‹‹ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ›› በሚል ርዕስ ሁለተኛዋ የሥነግጥም መጽሐፉ ታትማ ለንባብ በቅታለች። ነገር ግን በዚህ ወቅት ደበበ በሕይወት የለም ነበር። የዚህችን መጽሐፍ አጠቃላይ ገጽታ በተመለከተ አስተያየት የሰጠው ታዋቂው የወግ ጸሐፊና ሃያሲ መስፍን ኃብተማርያም ‹‹ደበበ ሰይፉ በርዕስ አመራረጡና በሚያስተላልፋቸው ልብ የሚነኩ መልዕክቶች ብቻ ሳይሆን በስንኞቹ አወራረድና የቤት



ደበበ ሰይፉ

አመታቱ በአጠቃላይ በውብ አቀራረቡ ተደራሲያንን የሚመስጥ ገጣሚ ነው። ስለ ተፈጥሮ ሲገጥም ፀሐይና ጨረቃ፣ ቀስተ ደመናና የገደል ማሚቶ ያጅቡታል። ስለ ፍቅር ስንኞች ሲቋጥር የፍቅረኞችን ልብ እንደ ስዕል ቆንጆ አድርጐ በቃላት ቀለማት ያሳያል። ክህደት ላይ እንደ አንዳንድ ገጣሚያን አያላዝንም። ይልቁንም ውበትና ህይወትን አገናዝቦ ‹ያውላችሁ ስሙት፤ እዩት› ማለትን ይመርጣል … እኔ እንደማውቀው ደበበ ሰይፉ በገጣሚነቱ ሁሌም ዝምተኛ ነው። አይጮህም። ጮሆም አያስበረግግም። ይልቁንስ ለዘብ ለስለስ አድርጐ "እስቲ አጢኑት" ይለናል። ደግመን እንድናነብለት የሚያደርገንም ይኸው ችሎታው ነው" በማለት ጽፏል። (በተጨማሪም፣ ለጥልቅ ሙያዊና ጥናታዊ ምልከታ የብርሀኑ ገበየሁን "የአማርኛ ሥነግጥም" መመልከት ይቻላል። የደበበን ስብስብ ስራዎች የያዘውና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ያብራራውን መጽሐፍም መመልከት ጠቃሚ ነው።)

ደበበ ከገጣሚነቱ ባሻገር ሃያሲም ነበር። ሃያሲ ታሪክ አዋቂ ነው። ያለፈውን ከአሁኑ ጋር እያነፃፀረ የሚያስረዳና የሚተነትን ባለሙያ ነው። የሂስ ጥበብን ከታደሉትና በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሂስ ጥበብ ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት ሃያሲያን መካከል ደበበ ሰይፉ አንዱ ነበር። ደበበ ያለፉ ታሪኮችንም ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር። በዚህም ምክንያት የሚሰጣቸው በሳል አስተያየቶች ከልብ የነበሩና ለለውጥ የሚያነሳሱ እንደነበሩ የሚያውቁት ሁሉ ይመሰክሩለታል። ደበበ ሰይፉ በሥነ ግጥም ተሰጥኦውና በሚያነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች በኢትዮጵያ የሥነጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ስማቸው ጐልቶ ከሚነሱ ከያኒያን መካከል አንዱ መሆኑን ቀደም ያሉት ኃያስያን ጽፈውታል።

የደበበ ችሎታ በዚህ ብቻም አያበቃም። ደበበ የትያትር ጥበብ መምህር ከመሆኑም በላይ በዘርፉ ውስጥ ግዙፍ የሚባል አስተዋፅኦ አበርክቶ አልፏል። ደበበ በመድረክ ላይ የሚሠሩ ቴአትሮችንና የቴአትር ጽሑፎች የያዟቸውን ጽንሰ ሐሳቦች (ኮንሴፕትስ) በመተንተንና ሂስ በመስጠት ለዘርፉ ዕድገት የበኩሉን ምሁራዊ ሚና ተጫውቷል።

ደበበ የቃላት ፈጣሪም ነው። ለአብነት ያህል በትያትርና በሥነጽሑፍ ዘርፎች ውስጥ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መጠሪያ የሆኑ ሙያዊ ቃላትን ወደ አማርኛ በማምጣት አቻ የሆነ የአማርኛ ትርጉም በመስጠት ይታወቃል። በኢትዮጵያ የሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ውስጥ እስከ አሁን ድረስ መጠሪያ የሆኑትንና ‹‹ገጸ-ባህርይ››፣ ‹‹ሴራ››፣ ‹‹መቼት››፣ ‹‹ቃለ-ተውኔት›› … እና የመሳሰሉትን ጽንሰ ሐሳቦች ያስተዋወቀን (ከመገኛ ቋንቋቸው ወደ አማርኛ ያሻገረው) ደበበ ሰይፉ ነው። ‹‹Character›› ለሚለው መጠሪያ ‹‹ገፀ-ባህርይ›› በማለት አቻ ትርጉም ሰጥቶታል። ‹‹Setting›› የሚለውና በውስጡ "ጊዜ" እና "ቦታን" መያዙን በመረዳት ‹‹መቼት›› ብሎ ተረጐመው። "መቼት" ማለት ‹‹መቼ›› እና ‹‹የት›› ማለት ሲሆን፤ ጊዜንና ቦታ (Time and Space)ን ይገልፃል። ‹‹Dialogue›› የሚለው ቃል ተዋንያን በትወና ወቅት የሚናገሩት ሲሆን፤ ይህን ቃል ‹‹ቃለ-ተውኔት›› በማለት በአማርኛ የተረጐመው ደበበ ሰይፉ ነው። ደበበ እነዚህንና ሌሎች በርካታ ሥነጽሑፋዊ (ኪናዊ) ቃላትን በመፍጠር ቃላቱ በትውልዶች አንደበት፣ አእምሮ እና ብዕር ውስጥ ለዘላለም እንዲኖሩ፤ ሙያው እንዲጎለብት ያደረገ ባለ ተሰጥኦ የጥበብ ሰው ነው።

ደበበ ለትያትር ትምህርት ዘርፍ ካበረከታቸው አስተዋፅኦዎች መካከል ለትምህርቱ መጐልበት ይረዳ ዘንድ በ1973 ዓ.ም. መጽሐፍ ማሳተሙ የሚጠቀስ ነው። መጽሐፏ ‹‹የቴአትር ጥበብ ከጸሐፌተውኔቱ አንፃር›› የሚል ርዕስ ያላት ስትሆን፣ በኢትዮጵያ የትያትር ሙያተኞች እንዲበራከቱና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሰፊ ድርሻ አበርክታለች፤ እስካሁንም ከ"መድረክ" ላይ አልወረደችም። ደበበ በዚህ ዘርፍ የተጻፉ የንባብ መጻሕፍት ያለመኖራቸውን ክፍተት ተገንዝቦ ክፍተቱት ለመሙላት ሙያዊ አሻራውን ያሳረፈ የዘርፉ ባለውለታ ነው።

ደበበ ጸሐፌ ፀሀፌ ተውኔትም ነበር። በርካታ ተውኔቶችን ጽፎ ለመድረክ አብቅቷል። አንዳንዶቹም ለበርካታ ጊዜያት ያህል በቴሌቪዥን ታይተውለታል። ደበበ ከጻፋቸውና ከተረጐማቸው ተውኔቶች መካከል ‹‹ከባህር የወጣ ዓሳ››፣ ‹‹እናትና ልጆቹ››፣ ‹‹እነሱ እነሷ››፣ ‹‹ሳይቋጠር ሲተረተር››፣ ‹‹የሕፃን ሽማግሌ››፣ ‹‹ክፍተት››፣ ‹‹እድምተኞቹ››፣ ‹‹ጋሊሊዮ ጋሊሊ›› … ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርና ተመራማሪ በነበረባቸው ዓመታት ከሰራቸው የምርምር ስራዎችና ከጻፋቸው መጻሕፍት መካከል፤

- የትያትር ጥበብ ከጸሐፊ ተውኔት አንፃር
- ደራሲው በአብዮት አውድ
- ዋዜማ ጦርነት ግጥሞች
- ሕዝባዊ ሥነግጥም
- Profile of Peasantry in Ethiopian Novels
- A Critical Analogy of Ethiopian Novels
- Foreign Scholars on Amharic Novels
- A Critical Analogy to Amharic Poetry
- The Need for Marxist Approach in the Teaching of Literature
- Post-Revolution Ethiopian Theaters …

የሚሉትና ሌሎች ስራዎቹ ይጠቀሳሉ።

በ1973 ዓ.ም ለአንባቢያን የቀረበው ‹‹ማርክሲዝምና የቋንቋ ችግሮቹ›› የሚለው መጽሐፉ ለሕትመት ከበቁ ስራዎቹ መካከል ተጠቃሽ ነው። በ1960 ዓ.ም. (ደበበ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበረበት ወቅት) ከታተሙ ሦስት አጫጭር ታሪኮች መድበል ውስጥ አንዱ የደበበ ሥራ ነበር።

ደበበ ሰይፉ ከእነዚህ ረቂቅ ከሆኑ ምሁራዊ አስተዋጽኦዎቹ በተጨማሪ በበርካታ ኪነጥበባዊ ጉዳዮች ላይም አሻራውን ያሳረፈ ምሁር ነበር። በቀድሞው ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ውስጥ በመሳተፍ ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ መስፋፋት ሰፊ እገዛ አድርጓል። በኢትዮጵያ ሬዲዮ ውስጥም የኪነጥበብ ዘርፍ ፕሮግራሞች አማካሪ ሆኖ ሰርቷል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የጥናት መጽሔት አሳታሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሆኖ አገልግሏል። የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ፕሬዝደንት በመሆንም ሙያዊ ኃላፊነቱን ተወጥቷል። እስከ ዛሬ የዘለቀችው ‹‹ብሌን›› የማኅበሩ የሥነጽሑፍ መጽሔት እንድትጀመርም አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪም በወቅቱ በርካታ የሙያው ባለቤቶች እንዲሰባሰቡና ከውጭ አገሮች፤ በተለይም ከሶቪየት ኅብረት ጋር ሙያዊ ድጋፍና ትብብር እንዲደረግም ጥሯል።

አንጋፋው ደራሲና ሃያሲ አቶ አስፋው ዳምጤ በአንድ ወቅት ስለ ደበበ ሲናገሩ ‹‹ደበበ ስራ ይወዳል፤ ስራው ጥንቅቅ ያለ ነው። … ለቴአትር ዲፓርትመንት ከመከፈቱ ጀምሮ መጽሐፍ ጽፎለታል። ጽንሰ ሃሳቡን እንዲረዱት አድርጓል። ስለ ደበበ ካስደነቁኝ አንዱ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታው ነው። የደራሲያን ማኅበር ሊቀመንበር ሆኖ እኔ ስራ አስፈፃሚ ሆነን ሠርተናል። ቀድሞ ከነበረው የማኅበሩ የሥራ ዘመን ያልታየ እንቅስቃሴ አድርጓል።" ብለውለታል።

አቶ አስፋው ‹እነሆ› የተሰኘች የአጫጭር ልብ ወለዶች እና ‹የጽጌረዳ ብዕር› የሚል የግጥም መድብል መድበሎች፤ እንዲሁም ‹ብሌን› የተሰኘች መጽሔት ታትመዋል›› ሲሉም የደበበን ሁለ ገብ ጥንካሬ ገልፀዋል።

ታዋቂው የወግ ጸሐፊና ሃያሲ መስፍን ኃብተማርያም ደግሞ ‹‹… ደበበ በጣም ጠንካራ፣ ትጉህ ሠራተኛ፣ ለተሰለፈበት ዓላማ ወደ ኋላ የማይል፣ በማስተማር [ተግባሩ] ፈጣሪ (Innovator) ዓይነት ነበር። የምናስተምረውን ኮርስ ‹እንዲህ ብናደርገው፣ እንዲህ ብንለው› እያለ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንድናሻሽል በማድረግ በኩል ፊር ቀዳጅ ነበር። … ደበበ ደራሲ ብቻ አይደለም። ጥሩ የማስተማር ችሎታም ነበረው›› በማለት የአይንና የተግባር ምስክርነቱን ሰጥቶለታል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነጽሁፍ መምህር የነበረው ብርሃኑ ገበየሁ በበኩሉ ‹‹… የደበበ አቀራረቡ ቀላልና የማያሻማ ነው። ድምፀቱ ደግሞ ሐዘን ከሰበረው ልብ የሚፈልቅ እንጉርጉሮ። የአቀራረብ ቀላልነት ውበቱ ነው። ይርጋለምና ልጅነቱ በተናጋሪው ህሊና አንድም ሁለትም ናቸው፤ የማይፈቱ›› በማለት ስለ ደበበ ሰይፉ ስራዎችና ብቃቱ በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ባሰፈረው ጽሑፉ ገልጿል። ደበበ ወንድሞቹና እህቶቹ ልክ እንደ'ርሱ አንባቢ እንዲሆኑ ይፈልጋል። ለታናናሾቹም መጻሕፍት እየገዛ ይሰጥ ነበር።

ደበበ ከ1985 ዓ.ም. በኋላ ዩኒቨርሲቲ አካባቢ ባሉ ሰዎችና ሁኔታዎች ማዘኑን ቤተሰቦቹ ይናገራሉ። ከግንቦት ወር 1985 ዓ.ም. በኋላ የማስተማር ስራውን አቆመ። ነገሮችን አብራርቶ ከመግለጽ ይልቅ ዝምታን መርጦ ለስድስት ዓመታት ያህል ቤት ውስጥ ዋለ። ከሰው ጋር የሚገናኝበት ዕድልም አልነበረውም። ‹‹ደበበ እንዴት ነህ?›› ሲባልም ‹‹ደህና›› ብሎ አጭር ምላሽ ከመስጠት ባሻገር የተብራራ ንግግር አይናገርም ነበር (በጣም ለሚወዱት ወላጅ እናቱ ግን መልስ ይሰጥ ነበር ተብሏል)።

በመጨረሻም በኢትዮጵያ የኪነጥበብ ዓለም ውስጥ ትልቅ ድርሻውን ያበረከተውና ምሳሌ መሆን የቻለው ገጣሚ፣ ፀሐፊ ተውኔት፣ ደራሲ፣ ሃያሲ፣ ተርጓሚ፣ መምህርና የሥነጽሑፍ ተመራማሪው ደበበ ሰይፉ ሚያዚያ 16 ቀን 1992 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ስርዓተ ቀብሩም ሚያዚያ 17 ቀን 1992 ዓ.ም በአዲስ አበባ ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ተፈፀመ። በወቅቱም በርካታ የሥነጽሑፍ ባለሙያዎችና የሕትመት መገናኛ ብዙኃን ስለደበበ ታላቅነት ደጋግመው አስነብበዋል፤ አስደምጠዋልም።

በአዲስ አበባ የሥነጽሁፍ መምህር የነበረው ገዛኸኝ ጌታቸው (አሁን ካናዳ ያለና በደበበ ሕይወትና ሥራዎች ላይ ስራዎችን እየሰራ የሚገኝ)፣ ደበበ ሰይፉ እንዳረፈ በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር። ‹‹ዛሬ የኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ አንድ ሊጋ ብዕር አጣ፤ ነጥፎ አይደለም ታጥፎ ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ የዋህ ሃሳብ አጣ። ከፍቶ አይደለም በኖ ተኖ እንጂ። ዛሬ ብዙዎቻችን ካወቅነው ብዙ ነገር አጣን። ካላወቅንም እሰየው፤ ከእንጉርጉሮና ከፀፀት ተረፍን።››

በ1995 ዓ.ም በጀርመን የባህል ተቋም ውስጥ በወይዘሮ ተናኘ ታደሰ አስተባባሪነት ዶክተር ፈቃደ አዘዘ፣ ዶክተር ዮናስ አድማሱ እና ገዛኸኝ ጌታቸው ‹‹የደበበ ሰይፉ ምሽት›› የሚል ደማቅ ዝግጅት አሰናድተውለት ነበር። ደራሲያኑ ነቢይ መኮንን፣ አበራ ለማ እና አብርሃም ረታ ቅኔ ዘርፈውለታል።

ደበበ በስራዎቹ ከሚታወቅባቸው አንዱ "ማህበራዊ ሂስ" (ሶሻል ክሪቲሲዝም)ን መሰረት ያደረጉት ስራዎቹ ሲሆኑ፤ በተመራማሪዎች ዘንድ አብዝተው ከሚጠቀሱለትም አንዱ፡-

**ጥሬ ጨው**
**መስለውኝ ነበረ**
**የበቁ የነቁ**
**ያወቁ የረቀቁ**
**የሰው ፍጡሮች**
**ለካ እነርሱ ናቸው**
**ጥሬ ጨው ጥሬ ጨው።**
**ጥሬ ጨዋዎች**
**መፈጨት፣ መሰለቅ**
**መደለዝ፣ መወቀጥ**
**መታሸት፣ መቀየጥ**
**ገና እሚቀራቸው፣**
**‹‹እኔ የለሁበትም››**
**ዘወትር ቋንቋቸው።**

የሚለውና ዘመን ተሻጋሪ ስራው ነው።
(ደበበ ሰይፉ፣ የብርሃን ፍቅር፣ 1971 ዓ.ም)

# ስፖርት



## ኢትዮጵያ አሁንም የማጣሪያ ጨዋታዎችን የማስተናገድ ፈቃድ አለማግኘቷ ተገለጸ

ብርሃን ፈይሳ

ለ34ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች የስታዲየሞችን ደረጃ እየገመገመ የሚገኘው የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን/ ካፍ/ የባህር ዳር ስታዲየምን በድጋሚ ገምግሞ ስታዲየሙ ጨዋታዎችን የማስተናገድ አቅም ላይ አለመድረሱን መግለጹን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አስታወቀ። ኢትዮጵያ ይህን ተከትሎ በሜዳዋ ማከናወን ያለባትን የማጣሪያ ጨዋታዎች በሌሎች ሃገራት ሜዳ ላይ የምታከናውን መሆኑን ገለጸ።

በርካታ ስታዲየሞችን በመገንባት ላይ ያለችው ኢትዮጵያ ግንባታቸው በተለያዩ ምክንያቶች ሙሉ ለሙሉ ባለመጠናቀቁ አለም አቀፍ ውድድሮችን የማስተናገድ አቅም ላይ አልደረሱም። በመሆኑም የአፍሪካ እግር ኳስን የሚመራው አካል /ካፍ/ ለባህርዳር ስታዲየም ጊዜያዊ ፈቃድ በመስጠት ውድድሮች ሲደረጉበት መቆየቱም ይታወሳል። በዚህም ስታዲየሞቹ መሟላት ያለባቸውን እንዲሟሉ ግንባታና እድሳት ላይ ያሉትም በሂደት እንዲጠናቀቁ እድል መገኘቱም ይታወቃል።

ይሁንና እድሳቶቹ እሱ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት እየተፈጸሙ አለመሆናቸውን ካፍ በመጥቀስም በጥቅምት ወር/2014ዓ.ም መስፈርቶቹ እስኪሟሉ ድረስ ኢትዮጵያ በሜዳዋ የምታደርጋቸው ጨዋታዎችን በገለልተኛ ሀገር እንድታከናውን ወስኖ በዚሁ ሲሰራ ቆይቷል። በዚህም መሰረት ከዚህ ቀደም ጨዋታዎች ሲደረጉበት የቆየው የባህርዳር ስታዲየም የተለያዩ ማሻሻያዎችን በማድረግ በድጋሚ ወደ ውድድር እንዲገባ ለማድረግ ሲሞከር ቆይቷል። ከእገዳው በኋላም በአማራ ክልላዊ መንግሥት የባህር ዳር ስታዲየምን በማሻሻል ውድድር የማስተናገድ ፈቃዱን መልሶ እንዲያገኝ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን ፌዴሬሽኑ ጠቁሞ ነበር።




ከመጫወቻ ሜዳ፣ የመገናኛ ብዙሃን ክፍል፣ የቪአይፒ፣ የተመልካች ፋሲሊቲ፣ የህክምና ክፍል እና ተያያዥ ግብዓቶች የተሰሩ ማሻሻያዎች ያሉቡት ሁኔታ በቅርቡ በካፍ በተወከለ የባለሙያዎች ቡድን ምልከታ ተደርጎበታል። ምልከታውን ተከትሎም ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር የምታደርገውን የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ሁለተኛ ጨዋታን ጨምሮ በቀጣይ በሜዳዋ የምታደርጋቸው ዓለም አቀፍ ጨዋታዎችን እንድታከናውን የሚያስችላት ግብረመልስ ሲጠበቅ ቆይቷል።

ካፍ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በላከው ሰባት ገጽ ያለው ሪፖርት ኢትዮጵያ የማጣሪያ ጨዋታዎችን በሜዳዋ የማስተናገድ አቅም እንደሌላት ማስታወቁን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ገልጿል። በቀጣይ የሚካሄዱ ጨዋታዎችም በየትኞቹ ሃገራት ሜዳዎች ለማድረግ እንደታቀደ እስከ ግንቦት 4 ድረስ እንዲያሳውቅም መጠየቁን አስታውቋል። በመሆኑም በቀጣዩ ዓመት ለሚካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ የሚደረጉት የማጣሪያ ጨዋታዎች በሌሎች ሃገራት ሜዳ ላይ የምታከናውን መሆኑን ፌዴሬሽኑ አረጋግጧል።

ሃገሪቷ በማጣሪያው የምድብ ድልድል በምድብ አራት ከግብጽ፣ጊኒ እና ማላዊ ጋር መደልደሏ ይታወቃል። እነዚህ ጨዋታዎች በደርሶ መልስ የሚካሄዱ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ሶስቱን የመልስ ጨዋታዎች በተለዋጭ ሜዳዎች ላይ የሚያደርግ ይሆናል።

በቀጣይ ሊደረጉ ስለሚገቡና ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት መሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶችም ካፍ በላከው ሪፖርት ተጠቁሟል። በዚህም መሰረት የመጫወቻ ሜዳውን በሚመለከት ሳሩ በአዲስ እንዲተካና በዘርፉ በሚሰራ አካል እንክብካቤ እንዲደረግለት፣ ተንቀሳቃሽ ግቦች እንዲኖሩት፣ የጨዋታ አመራሮች እና የአሰልጣኞች ስፍራ አለም አቀፍ ደረጃን ያማከለ እንዲሆን እንዲሁም የምሽት መብራትን የሚያካትቱ ስራዎች እንዲከናወኑ ድምዳሜ ላይ መድረሱ ታውቋል።

የመልበሻ ክፍልን በሚመለከትም የካፍን መስፈርት እንደማያሟላ ሪፖርቱ አመልክቶ፣ ሙሉ ለሙሉ እንዲቀየር፣ የማሟሟቂያ ክፍሉ በሰው ሰራሽ ሳር እንዲተካ፣ የካፍ ቢሮ እንዲታደስ እንዲሁም የኳስ አቀባዮችና ባንዲራ የሚይዙ ታዳጊዎች ክፍል እንዲዘጋጅም በሪፖርቱ ተመላክቷል። ከህክምና ክፍል ጋር በተያያዘም አስፈላጊ የሆኑ 23 ቁሳቁሶች እንዲሟሉ፣ የአበረታች ንጥረነገሮች መቆጣጠሪያ ክፍል ከመልበሻው አቅራቢያ እንዲሆንና አስፈላጊ ሁኔታዎች እንዲሟሉም ካፍ አሳስቧል።

ተመልካቾችን በሚመለከትም ጣሪያ፣ ወንበር፣ የመዝናኛ፣ የደህንነትና የመቆጣጠሪያ፣ የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና መስጫ፣ ግዙፍ ስክሪን እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች አመቺ ሆኖ መዘጋጀት እንዳለበት ተገልጿል። የክብር እንግዶች ክፍልም ምቾት ባለው ሁኔታ እንዲዘጋጅ እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ክፍል አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች እንዲሟሉ እና ጋዜጣዊ መግለጫ የሚሰጥባቸው ስፍራዎች መካተትም እንዳለባቸውም ተጠቁሟል።

የልምምድ ሜዳውም መብራት እና ቢያንስ አንድ ቡድን ማስተናገድ የሚችል ክፍል ያለው እንዲሆን፣ የአንቡላንስ አቅርቦት እንዲሁም ደህንነቱ የተጠበቀ መግቢያና መውጫ እንዲኖረውም ተመላክቷል።

በሪፖርቱ የባህርዳር ስታዲየም ለሆቴል እና ሆስፒታል ያለው ቅርበት በመስፈርቱ መሰረት በቂ መሆኑም ተጠቁሟል። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽንም የአማራ ክልል መንግሥት ስታዲየሙ መስፈርቶችን እንዲያሟላ ሲያደርግ ለቆየው ከፍተኛ ጥረት ምስጋናውን አቅርቦ፤ በቀጣይም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን በሃገሩ እንዲጫወት ጥረት ማድረጉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቋል።


# INVITATION FOR BID

1. The South Western Ethiopia Peoples Regional State HEALTH BUREAU invites registered contractors with license renewed for the year 2014 E.C and registered for VAT to submit sealed bids for providing the necessary labor, materials and equipment for the construction of Different Health Institutions as follows.

| No | Name of Project | Location | | Category | BID BOND |
|---|---|---|---|---|---|
| | | Zone/S. woreda | Woreda /Town | | |
| 1 | Teppi General Hospital Sheka Expansion | Sheka | Teppi | GC-5 and/or BC-5 & above | 300,000 |
| 2 | Yadota Health Center Expansion | Kaffa | Saylem | GC-5 and/or BC-5 & above | 100,000 |
| 3 | Bonga Blood Bank Completion | Kaffa | Bonga | GC-5 and/or BC-5 & above | 100,000 |

- A bidder can purchase one document only.
- **NB.** Bidder with poor efficiency on any projects in the region, having black listed in the region for poor performance. (Whenever recognized will automatically be rejected).those who successfully complete the above individual as well as packaged projects should provide all the necessary documents including provisional letter of acceptance included with their qualification document.
- Bid bonds should be incorporated within the original envelope of the technical document or separately sealed.
- All bidders are advised to visit site before fixing rate.
- Every page of technical documents to be submitted need to be properly structured, clearly visible and non-erased. submittal of any clearly invisible document(technical document) by any bidder would be considered void during evaluation
- Any copy document to be submitted need to be clearly visible in order to be considered for evaluation.
- Due to not giving pages properly to technical documents or missing of pages during submittal of technical documents the client would not be responsible.
- To qualify for the award of the contract the bidder is required to fulfill the minimum qualification criteria which are provided in bidding document.
- Bidding will be conducted through the standard Bidding Document (SBD) for procurement of works For National Competitive Biddings (NCB) prepared by the Federal Public Procurement and Property Administration Agency, 2011.

2. Interested eligible bidders may obtain further information and inspect the bidding document at the Office of:

**SWERPS HEALTH BUREAU**
**Procurement, Finance & Property Administration Sub Process**
**Room No**
**Tel.251917004484**
**Bonga**
**Ethiopia**

3. Bidders are instructed to submit "One Original" and "Two copies" of Technical and Financial Documents in different folder. Labeled as ORIGIONAL AND COPY FOR BOTH PROPOSALS PROPERLY, separately and shall be sealed in large outer mother envelope.
4. A complete set of bidding documents may be purchased by any interested eligible bidder on the submission of written application to the above address and payment of a non-refundable fee of Birr 500.00 (Five Hundred) for each of document starting from the first appearance of this advertisement on the Ethiopian Herald for 21 calendar days. The final submission date and opening of the technical proposal will be on 22nd date of this announcement at 3:00-5:00 & 8:30 local time respectively. If the 22' day is not a working date, it will be held on the next working day.
5. All Bidders must be accompanied by a bid security of Ethiopian Birr as stated above in the table. The bid security shall be payable on demand to the bureau and must be an irrevocable letter of credit, or Bank Guarantee, or a certified payment Order (CPO) at the bidders option sealed with Original Technical proposal.
6. Evaluation is to be carried out in two stages, Qualification application first and financial document of qualified bidders next.
7. Bids will be opened in the presence of bidder's Legal representatives who choose to attend at the SWERPS HEALTH BUREAU Meeting hall.
8. Bidders shall submit original financial audit report which is audited by external certified Auditor sealed with technical document and it must be sealed separately and if the audit is audited by an accountant it will not be considered.
9. The SWERPS HEALTH BUREAU reserves the right to reject all or parts of bids.

**For reference the address:-SWERPS HEALTH BUREAU**

**South Western Ethiopia Peoples Regional State HEALTH BUREAU**